# ጥላ TILA

ጥላ ጥር 2005 ዓ.ም ነኛ ዓመት ቁ 5 ልዩ እትም TILA January 2013 1st Year 5th Spe. Edition

## በኢህአዴግ ውስጥ የተፈጠረውን ክፍተት ልንጠቀምበት ይገባል።

አቶ ግደይ ዘርዓፅዮን



የጥላ መፅሄት አንደኛ ዓመት ልደት
በዓል ልዩ ቃለ-ምልልስ
ከኖርዌይ






# East Africa stagnates near bottom of the index, Ethiopia 137th

Despite the release of two Swedish journalists arrested in 2011,**Ethiopia**(137th) fell ten places because of its repressive application of the 2009 anti-terrorism law and the continued detention of several local journalists.

# ጥላ


| | |
|---|---|
| **ዋና ስራ አስኪያጅ** | **General Manager** |
| መስፍን አብርሃ | Mesfin Abraha |
| | |
| **ዋና አዘጋጆች** | **Editor In Chiefs** |
| እየሩሳሌም ሱሞሮ | Eyerusalem Sumoro |
| ብሩክ ገ/መስቀል(ካርቱኒስት) | Biruk G/Meskel(Cartoonist) |
| ዳዊት ፋንታ | Dawit Fanta |
| | |
| **አዘጋጆች** | **Editors** |
| ዮሃንስ ሳምሶን | Yohanes Samson |
| ደበበ ከበደ | Debebe Kebede |
| ፍስሃፅዮን ሃይለገብርኤል | Fisshatsion Hailegeberile |
| **ፅሁፍ አስተባባሪዎች** | **Coordinators** |
| ብርሃኑ ባዩ | Berhanu Baue |
| ኤደን ዳዊት | Eden Dawit |
| አስናቀች ጥላሁን | Asnakch Telahun |
| ህይወት ጥላሁን | Hiwot Tilahun |
| ወልደኪሮስ አስፋው | Weldekiros Asfaw |
| **የኮምፒዩተር ፅሁፍ ቅንብር** | **Computer Graphics** |
| ህሊና ዳዊት | Hilina Dawit |
| ዘውድነሽ ንጋቱ | Zewdinesh Nigatu |



**የጥላ መፅሄት አድራሻ/Tila Magazine Address**

**Mesfin Abraha**
**Löhrgasse 4**
**36251 Bad Hersfeld**
**Email:- tilamagazine@yahoo.de**
**Web-Site:- tilamagazine.yolasite.com**
**Tel.No.:- 015222195567,017659384456**
**017668830082, 017671668780**

# ማውጫ


| | ገጽ |
|---|---|
| ክፍተቱን እንጠቀምበት/ቃለ-ምልልስ/ | 7 |
| የደም መንግስት | 10 |
| ድምፅ አልባው አመፅ | 11 |
| ማን ያውራ የነበረ | 11 |
| የኢትዮጵያ ሴቶች ...... | 12 |
| አሁንም ምርጫው.... | 12 |
| በአሁኑ ወቅት | 12 |
| መፍረሱ አይቀርም | 12 |
| የወያኔ አገርንና..... | 12 |
| ይብቃ በፍርሃት መኖር | 13 |
| አይ አገሬ | 13 |
| ለወሳኙ ድል እንነሳ | 13 |
| መንግስት ከእምነት ተቋማት.... | 13 |
| የኢትዮጵያ ትንሳኤ አሁን ነው | 14 |
| ዴሞክራሲ የሚከበርበት አገር... | 14 |
| ማስገደድ ወይም ማስወገድ | 14 |
| ኦሮሚያ ነፃ እስክትወጣ... | 14 |
| አሁንም የጋራ ትግል | 16 |
| የወያኔ የጥፋት አገዛዝ | 16 |
| ቤል ተዋረደ ናባው ፈራረሰ | 16 |
| የኢህአዴግ ካድሬዎችና ፖሊስ.... | 16 |
| የለውጥ ጊዜ ተቃርቧል | 17 |
| ስደት እስከመቼ? | 17 |
| ከአምባገነንነት ወደ አምባገነንነት | 17 |
| መሪ የሌለው መንጋ ይበተናል | 17 |
| በኢህአዴግ ስርዓት የለም ተጠያቂነት | 17 |
| ታሪክን እንጠብቅ | 18 |
| የኢትዮጵያ ህዝብና...... | 18 |
| መለስ ከመቃብር ሆኖ...... | 18 |
| የፕሬስ አፈናው ይቁም | 18 |
| ወያኔና የፍትህ ስርዓቱ | 18 |
| አንቀፅ 27 የወረቀት ላይ ነብር | 18 |
| የምን ምርጫ ? | 19 |
| አፈና ለነፃነት | 19 |
| በተባበረ ክንድ ... | 19 |
| ነፃነትን የማያውቅ.... | 19 |
| በህብረት እንቁም | 19 |
| ወያኔ ሆይ | 20 |
| ዲክታተሩ | 20 |
| The real behavior …... | 20 |
| Civic society……….. | 20 |
| EPRDF stop…… | 21 |
| Freedom&Democracy….. | 21 |
| The failures of ´Meles | 22 |
| ስፖርት በአፍሪካ ዋንጫ ዙሪያ | 24 |

# About Tila

Realizing the fact that the digital age has empowered and made ordinary people across the world irrepressible beyond their imagination, **WE** aims to serve as a credible platform that will spread uncensored interviews, news, commentaries and analyses that are unlikely to see daylight in Ethiopia.

Fortunately, here is where you find **TILA**, the un-disputably best source of information serving the Ethiopian Diaspora community in Europe & America with a proven record of excellence in journalism.

TILA is a political magazine published and distributed by patriotic Ethiopians around Hessen region in Germany. Tila appears in Amharic, English and Germany Languages every 3 months. It is a magazine of quality, responsibility and standard. Entertainment and sport are among our coverage issues next to Ethiopian politics.

As a reader, you are to get useful political and current news in **TILA** than any other publication can offer you. More comprehensive analysis and interpretations than any other media can present to you. In fact, these are some of the qualities of **TILA** that has made it the largest circulating magazine in its category. **TILA** magazine has also partnered with ethiomedia.com, ethiogermany.de, ethiopiazare.com and afroaddis.wordpress.com among others, to deliver reliable and high quality content to our visitors.

Don’t take the chance of missing this spectacular political magazine. Subscribe to it today! We promise, you won’t regret your decision. Reach us on tilamagazine@yahoo.de & tilamagazine.yolasite.com

**Tila Magazine is yours Magazine!**


## ውድ አንባብያን

**ጥላ** መፅሄት በየሶስት ወሩ የሚታተም የፖለቲካ መፅሄት ነው።መፅሄቱ የኢትዮጵያን ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ መሰረት አድርጎ በጀርመን አገር የሚታተም ቢሆንም መረጃ መረቦችን በመጠቀም መላውን ዓለም የማዳረስ ዓላማን አንግቦ እየተንቀሳቀሰ ነው።

የአገራችንን ወቅታዊ ሁኔታና ጠቃሚ መረጃዎችን በማካተት ዝናን ያተረፈው የጥምረት መፅሄት አዘጋጆች ያቋቋሙት ጥላ መፅሄት የስሙ ስያሜ እንደሚያመለክተው የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ሃይሎች በተበታተነ ሁኔታ የሚያካሂዱትን የትግል ሂደት በማስቀረት በአንድ ጥላ ስር እንዲሰባሰቡ ለማሳሰብና አቅጣጫ ለመጠቆም ነው።

የፖለቲካ ሃይሎች በተበታተነ ትግላቸው ጋት እንኳን መራመድ እንደማይችሉ በመገንዘብ የጋራ ትግል እንዲያካሂዱ ለማበረታታትም ጭምር ነው እ.ኤ.አ ከጥር 2012 ጀምሮ በዚህ ስም መፅሄቱ እንዲጠራ የወሰንነው።በመፅሄቱ አዝናኝና አስተማሪ ዝግጅቶች የሚካተቱበት ሲሆን ስፖርትም ትኩረት ያገኛል። **ጥላ** መፅሄት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሃሳቡን ያለምንም ገደብ በነፃነት የሚያቀርብበት ክፍት መድረክ በመሆኑ በመፅሄቱ የሚወጡት ፅሁፎች በሙሉ የፀሃፊዎቹን እንጂ የጥላ መፅሄት ዝግጅት ክፍልን የማይመለከቱ መሆናቸውንም መግለፅ እንወዳለን።

**ጥላ መፅሄት የእናንተው መፅሄት ናት!**



# EDITORIAL



## WE DON´T GIVE UP TO FIGHT!

Almost from the end of the 1991, politically conscious Ethiopians had been attracted to modern civil rights, especially the freedom of the press. As early as 1993, Ethiopian Journalists had asked the ruling party to left the regulation restricting the freedom of the press.

Following the 1993 press freedom regulation which was enacted by the transitional government gives an opportunity to Ethiopians to express their feeling openly. But, especially after the 2005 election things are become very difficult like the previous military regime. To be a journalist is often to be a political worker& an agitator at considerable self-sacrifice.

Based on the above core facts, we were tried to tackle the challenges we had back home. Unfortunately, we couldn`t manage it, Because of the carrot and stick system of the ruling anti-democratic government of Ethiopia. Currently, free journalists are suffering a lot because of the new anti-terrorism ´´Journalism´´law. (the law, which suppressed freedom of expression or the right to know).


Even though, we are now in a free country, we tried our best to assure the real freedom of expression in our homeland. Thanks God, **TILA MAGAZINE** is now becoming the voice of the voiceless in& outside Ethiopia.

Nevertheless, our end goal is to push the Ethiopian regime to accept & respect freedom of press & expression as the key points of human rights.

When we are celebrating our first year anniversary, we don`t forget to thank our readers in general and special thanks to **TILA** Magazine staff, ethiomedia.com, ethiopiazare.com and etc for their remarkable support. Without yours support, **TILA** was growing like a carrot.

**TILA** Magazine has as usual a special guest of honor and current articles. Have a nice reading.

**TILA Magazine is yours Magazine!**
**TILA is a Multi-lingual Magazine not only you read it, but also you will write on it!**



# ርዕሰ አንቀፅ



# ትግላችንን አናቆምም !

ኢህአዴግ መራሹ ሃይል ገና ደርግን በሃይል እንደገረሰሰው በ1983ዓ.ም መጨረሻ ግድም ነበር የፖለቲካ ዕውቀቱ ያላቸው ተራማጅ ኢትዮጵያውያን አዲሱ ስርዓት የሲቪል መብቶች በተለይም የፕሬስ ነፃነትን እንዲያውጅ መገፋፋት የጀመሩት።በ1985 ዓ.ም መጀመሪያ አካባቢም በመላው ዓለም የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ጋዜጠኞች መንግስት በቀድሞው ስርዓት ታውጆ የነበረውን ፀረ-ፕሬስ ህግ እንዲያነሳላቸው ጠይቀዋል።

በሽግግር መንግስቱ በ1985ዓ.ም የወጣውን የፕሬስ ህግ ተከትሎ ታዲያ በርካታ የፕሬስ ውጤቶች ታትመው ህዝቡ በአንፃራዊ ነፃነት ሃሳቡን በይፋ መግለፅ ጀምሮ ነበር። ነገር ግን በተለይ ከ1997ቱ ምርጫ በሁዋላ ነገሮች ሁሉ ልክ እንደ ደርጉ ስርዓት ከባድ ሆኑ። ጋዜጠኛ መሆን ማለት የፖለቲካ ሰራተኛ ወይም የስርዓቱ ቀስቃሽ በመሆን ራስን ለውርደት አሳልፎ መስጠት እየሆነ ነው ያለው።ጋዜጠኛው የራሱን ሙያዊ ስራ ትቶ የበረከት ስምኦንን ስራ እየሰራለት ነው የሚገኘው።

ይህንን አንኳር እውነታ መሰረት በማድረግ በአገር ቤት እያለን በሙያው ላይ የተጋረደውን አደጋ ለመከላከል እንደ አቅሚቲ ሞክረናል።ግን አንድ ወቅት አቶ መለስ እንዳሉት የበዛ መሳሪያ ያለው በሚለው ህግ ብዕርና ጥይት ስላልተመጣጠኑ ሊሳካልን አልቻለም።አሁንም ቢሆን በርካታ የነፃው ሚዲያ ጋዜጠኞች በፀረ-ሽብርተኝነት (ጋዜጠኝነት) በሚባለው ህግ በሰበብ አስባቡ ለእስር ለስደትና ለእንግልት እየተዳረጉ ናቸው።

ምንም እንኳን እኛ በነፃይቱ አገረ ጀርመን ብንኖርም በአገራችን ያለውን የፀረ-ጋዜጠኛ ስርዓት በማረም ወይም ለአራሚ አጋልጦ በመስጠት ትክክለኛው ሃሳብን በነፃ የመግለፅ መብት እንዲረጋገጥ ጥረታችንን እንቀጥላለን።ምስጋና ለእግዚአብሄር ይሁንና ጥላ መፅሄት በአገር ውስጥም ይሁን በውጭ ላሉና ድምፃቸው እንዳይሰማ በስርዓቱ የታገዱ ኢትዮጵያውያን ድምፅ ለመሆን በመብቃታችን ኩራት ይሰማናል።

ይሁን እንጂ የመጨረሻው ግባችን በኢትዮጵያ ያለው መንግስት ሃሳብን በነፃነት የመግለፅና የፕሬስ መብቶች የሰብዓዊ መብት ዋነኛ ነጥቦች መሆናቸውን አምኖ ከልብ እንዲቀበልና እንዲያከብር መግፋት ነው!

አንደኛ ዓመታችንን ስናከብርም ከፍተኛ ድጋፋቸው ላልተለየን ለአንባቢዎቻችን በተለይ ደግሞ ለጥላ መፅሄት ባልደረቦች ለኢትዮ ሚዲያ ዶት ኮም፤ ለኢትዮጵያ ዛሬ ዶት ኮምና ለሌሎችም ታዋቂ መገናኛ ብዙሃን አጋሮቻችን ምስጋናችን ከልባችን ነው።ያለእናንተ ድጋፍ የጥላ እድገት የማይታለም ነበርና።

**ጥላ** መፅሄት እንደተለመደው ልዩ የክብር እንግዳን ጋብዛ በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ አወያይታለች።ወቅታዊ ጉዳዮችም ተካተዋል። መልካም ንባብ! ምኞታችን ነው አብረን እንዝለቅ!

**ጥላ መፅሄት የእናንተው መፅሄት ናት! "ጥላ የሚያነቧት ብቻ ሳትሆን የሚፅፉባትም መፅሄት ናት"**


It's our very
first Anniversary



# በመለስ ሞት የተፈጠረውን ክፍተት ልንጠቀምበት ይገባል!

**አቶ ግደይ ዘርዓፅዮን**
**የኢትዮጵያ ህዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ ዋና ፀሃፊ**

የዛሬው የጥላ አንደኛ ዓመት ልዩ የክብር እንግዳ አቶ ግደይ ዘርዓፅዮን ይባላሉ።አቶ ግደይ ህወሓትን ከፈጠሩት ጥቂት ግለሰቦች ውስጥ የአንበሳውን ድርሻ ይይዛሉ።እሳቸው ታዲያ እስካሁን የእድሜያቸውን ሁለት ሶስተኛ በኢትዮጵያ ትግል ውስጥ በማሳለፍ ላይ ናቸው።አገራችን ውስጥ ባላቸው የፖለቲካ ህይወት ልምድ ከጠገቡትና አንቱ ከሚባሉት በጣም ጥቂት ሰዎች መካከልም እጅጉን ቦታ የሚሰጠው ስፍራ አላቸው።

የቀድሞውን የፊውዳል ስርዓት ከመቃወም ጀምሮ ደርጉንም በማፍረክረክ ከተሰሩት ታሪኮች አብዛሃኛው ላይ የእሳቸው አሻራ አለበት። የተወለዱት በፈረንጅ አቆጣጠር በ1950 ዓም ነው፡፡ በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍለሃገሮችም አድገዋል። ተምረዋል፡፡ በቀድሞው አፄ ሃይለስላሴ/የአሁኑ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እአአ ከ1968 - 1974ዓ.ም ቆይተዋል፡፡በተለያዩ ክልሎች ማደጋቸውና መማራቸውም የኢትዮጵያን ፖለቲካ በቀላሉ ለመረዳትና ብሔራዊ አስተሳሰብ ያላቸው ሰው እንዲሆኑ እንዳደረጋቸው ብዙዎች ይስማማሉ።የተለያዩ የአገሪቱን ወቅታዊ የፖለቲካ ሁኔታ በተመለከተ ብዙዎች መፅሃፍ ሲያገላብጡ ጊዚያቸውን ከማጥፋት ይልቅ አቶ ግደይ ጋር በመደወል ወይም በአካል በመገናኘት የካበተ ልምዳቸውን በማስረጃ አስደግፈው ማግኘት እየቀለላቸው ከመጣ ውሎ አድሯል።

ህወሓትን ከፈጠሩት ጥቂት ግለሰቦችም መካከል አንዱ ናቸው።ከህወሓት ጋር በደርጉ ዘመን ከተለያዩ በሁዋላም ከአገር በመውጣት በተቃዋሚው ጎራ ተሰልፈው በመታገል ላይ ናቸው።በአሁኑ ወቅት ደግሞ የተቃዋሚውን ጎራ ባንድ ጥላ ለማሰባሰብና ጠንካራ ሃይል ለመሆን በቅርቡ ከስምንት ፓርቲዎች ተውጣጥቶ የተቋቋመውን "የኢትዮጵያ ህዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ" በዋና ፀሃፊነት በመምራት ላይ ናቸው።

እኛም ወቅታዊውንና ያለፈውን ታሪክ እያጣቀሱ ለአንባብያን በቂ እውቀት እንዲያስጨብጡልን ከሚገኙበት ከኖርዌይ ተከታዩን ቃለ-ምልልስ አድርገናል። ጠቃሚ መረጃዎች ከተካተቱበት ከዚህ ውይይት በርካታና ሁለገብ መረጃዎች እንደምታገኙ እምነታችን ነው።ቃለ-ምልልሱን ጋዜጠኛ መስፍን ኣብርሃ አዘጋጅቶታል። መልካም ንባብ!

**ጥላ፡-** ህወሓትን ከመመስረታችሁ በፊት ማገብትን መስርታችሁ ነበር።እርሶ ደግሞ ሁለቱንም ድርጅቶች ከፈጠሩት ጥቂት ሰዎች አንዱ ነዎት ዛሬ ደግሞ ሌላ ካምፕ ውስጥ ነው የሚገኙት።የፈጠሩትን ድርጅት መልሶ መቃወም አይፈታተንም ወይ?



**አቶ ግደይ፡-** እርግጥ ማገብትንና ከዝያም ቀጥሎ ህወሓትን በመመስረት ከጀማሪዎቹ አንዱ ነኝ ሆኖም ድርጅቱ ከተመሰረተበት ዓላማና አሰራር ውጭ ሲሆን እስካላመንኩበትና እስካልተቀበልኩት ድረስ የፈጠርኩት ስለሆነ አብሬ የሙጥኝ ማለት ትክክል አይደለም፡፡ ጎሊናየ ቀናና ትክክል ነው ብሎ በሚያምንበት መስመር ላይ እስከቆምኩ ድረስ ማንኛውንም ፈተና ለመቋቋም ዝግጁ ነኝ፡፡ በእምነቴ ብቻየን የምቆምበት ጊዜ በህይወቴ ብዙ ጊዜ አጋጥሞኛል ሆኖም ትክክልነታቸው በጊዜ እየተረጋገጠ ሲመጣ ሁላችንም እንማርበታለን እኔም እረካበታለሁ፡፡ አቋሜ ትክክል በማይሆንበት ወቅትም ከድክመቴ እማርበታለሁ የሚል እምነት አለኝ፡፡ ከሁሉም በላይ ግን ልዩነትን ማክበር ዲሞክራሲያዊና ሰብኣዊ መብት ስለሆነ የጎሊና እረፍት ይሰጠኛል፡፡

**ጥላ፡-** ገና በአፍላነት ዕድሜያችሁ የማይገፋ የሚመስለውን ተራራ ለመናድ ዓላማ ሰንቃችሁ ድርጅት መስርታችሁ ወደ ትግል ገብታችሁ እልፎችን ካሰለፋችሁና ከመራችሁ በሁዋላ ከእናንተ በሁዋላ በመጡ ሰዎች ከፈጠራችሁት ድርጅት እንዴት ለቀቃችሁ?በእውነት ከእነመለስ ቡድን ጋር ያለያያችሁ ትክክለኛ ምክንያት ምን ነበር?

**አቶ ግደይ፡-** እኔና ዶክተር አረጋዊ ከድርጅቱ የለቀቅነው በፖለቲካ ሴራ ነው፡፡ በሴራው ከኛ በኍላ የመጡት ብቻ ሳይሆን ከኛ ጋር መስራች የነበሩት እነ ስዩም መስፍንና አባይ ጸሃየም አሉበት፣ ከነዚሁ ጋር የሴራው ዋና መሪዎች ስብሓት ነጋ፣ ስየ አብረሃና መለስ ዜናዊ ናቸው፡፡ መነሻው የስልጣን ፍላጎት ሲሆን ከኔ ጋር ለነበረው ልዩነት የፖለቲካ ልዩነት በሚል እንደሽፋን ተጠቅመውበታል፡፡ የተነሱት ፖለቲካዊ ልዩነቶች ኣንዳንዶቹ ወቅታዊ ያልሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ የማያምኑበትን ግን ከኔ ጋር ልዩነት ለመፍጠር ሆን ብለው የተወሰዱ አቋሞች ነበሩ፡፡ የስታሊንና የሆጃ ተከታዮች በመሆናቸው የዲሞክራሲን ጥያቄ አስመልክቶ ከኔ ጋር ትልቅ ልዩነት ነበር፡፡ ሌላው ልዩነታችን በታክቲክና በስትራተጂ ያለው ግኑኝነት በሚመለከት ሆኖ በተግባር ሲተረጎም በውጭ ጉዳይ ፖሊሲ፣ በኢትዮጵያውያን ታጋይ ኀይሎች የግንባር ጥያቄ በሚመለከት፣ ከህዝባዊ ግንባር ጋር የነበረ ግኑኝነት በሚመለከት የመሳሰሉ ነበሩ፡፡ ይህም ቢሆን እነ መለስ እየተውላገዱም ሆነ እየተደናበሩ እኔ ያልኩትን አመለካከት እየተከተሉ በመሄዳቸው በየጊዜው ' ግደይ የሚለው ይህን አልነበረም ወይ ' የሚለው ጥያቄ እየተነሳ ያስቸገራቸው መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ይህ ጉዳይ ሰፊ ስለሆነ በዚሁ ቃለመጠይቅ ለመዘርዘር አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ በዚሁ ላይ የጻፍኳቸው ጽሁፎች በእጅ የተጻፉና በትግርኛ ስለሆኑ ለአንባቢያን በስፋት ለማቅረብ ጊዜ አላገኘሁም፡፡

**ጥላ፡-** እነሱ የእናንተ ሃሳብ ተራማጅ ያልሆነ ስለነበር በውይይቱ ወቅት ሃሳባችሁ

ተሸንፎ በክብር እንዳሰናበቷችሁ ነው የሚናገሩት።እርሶ ምን ይላሉ?

**አቶ ግደይ፡-** ይህ ውሸት ነው እርግጥ አልገደሉኝም አላሰሩኝም የነበረው ሁኔታ ግን በጣም አስጊና ኢ-ዲሞክራሲያዊ ነበር፡፡ ከትግርኛ ጽሁፎቼ አንዱ የሚከተለውን ብትመለከቱ ሁኔታውን በስፋት ይገልጸዋል፣

http://www.tand-tesfana.webs.com/Ghidey-MLLT2.pdf



**ጥላ፡-** በወቅቱ ከህወሓት ጋር ሲለያዩ ምን ነበር የተሰማዎት?የታጋዩ ስሜትስ ምን ነበር?

**አቶ ግደይ፡-** ህወሓት በስልጣን ሽኩቻና በተሳሳተ መስመር መግባቱ በጣም ነበር ያሳዘነኝ፡፡ ካድሬውም የተፈጠረውን ሁኔታ ለመገንዘብ አለመቻሉና ፈሪ መሆኑን ስገነዘብ ለዚሁ ድክመት ከተጠያቂዎቹ አንዱ መሆኔንና የሰራነውስ ድክመት የቱ ላይ ነው የሚለውን እንድመለከት አድርጎኛል፡፡ በዚሁ ጉዳይ ታጋዩ እንዳዘነና እንዳልተቀበለው እስካሁንም ድረስ በተለያዩ መልክና ሁኔታዎች ጥያቄ እያነሳባቸው መሆኑ የሚታይ ሃቅ ነው፡፡

**ጥላ፡-** እናንተ ከምስረታው ጀምሮ የታገላችሁለት ህዝባዊ ዓላማ እንዴት ተጓዘ?አሁን የደረሰበት ደረጃስ የታገላችሁለት ነበር ወይ?ምን ጎደለው?

**አቶ ግደይ፡-** ህወሓት ትግሉን ሲጀምር በወቅቱ ሲነሱ የነበሩትን ጥያቄዎች የብሄሮች እኩልነት፣ መሬት ለአራሹ፣ የዲሞክራሲ መብቶች የመናገር የመጻፍ የመደራጀት፣የዲሞክራሲያዊ መንግስት መመስረት፣ የሚሉትን አንግቦ የደርግን ወታደራዊ መንግስት በትጥቅ ትግል ለመጣል ነበር የተሰለፈው፡፡ በ1984 እኔ እስከለቅ ድረስ ህዝብን በማደራጀት ሰፊ ነጻ መሬት በማውጣትና አስተዳደሮችን በመመስረት፣ የህወሓት ሰራዊት ደግሞ ከደባይና ከተከላካይ ደርጃ ወጥቶ ወደ አጥቂነት የተሸጋገረበት ደርጃ ላይ ደርሶ ነበር፡፡ በመጨርሻም ደርግን አሸንፎ ስልጣን ይዟል፡፡ የተነሳንባቸውን የብሄሮች እኩልነትና የዲሞክራሲያዊ መንግስት መመስረት ጥያቄ ግን አላሟላም ብቻ ሳይሆን ጨቋኝና አፋኝ የሆነ የጠባብ ብሄርተኛ ስርዓት መስርቷል፡፡

**ጥላ፡-** ህወሓት ከትግሉ ጀምሮ ዴሞክራቲክ ነበር ወይ?በድርጅቱውስጥ ጤናማና የተስተካከለ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብና አካሄድ ነበር ማለት ይቻላል?

**አቶ ግደይ፡-** ትግሉ ሲጀመር ሁሉም የሚተዋወቅና የተማረ ስለነበር ውይይትም ውሳኔዎችም በግልጽና በጋራ አመራር የሚወሰኑ ፍራቻ የሌለበት ዲሞክራቲክ ነበር፡፡ ዲምክራቲክና ሰብአዊ መብቶች አመልካከታችን በማርክሲስት ሌኒንስት ስነሃሳብ የታጀበ ስለነበርና በህብረተሰባችን የነበረን ተሞክሮ ጋር በማዛመድ የቱን ያህል ብስለትና ዲሞክራሲያዊ ባህል ነበረው የሚለው ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ነው፡፡ ድርጅቱ እያደገ ሲሄድና በትግልም እያጋጠሙት በሄዱት ችግሮችና ኢንዲሁም ወታደራዊ ድርጅት በመሆኑ ወታደርዊ ዲሲፕሊን እየገዛው በመሄዱ የነበረው ዲምክራቲክ ሁኔታ እየተሸረሸረ መሄዱን እናያለን፡፡ ይህንን በሚመለከት በስፋት እላይ በጠቀስኩት ጽሁፍ ላይ ገልጫለሁ፡፡

**ጥላ፡-** በትግሉ ወቅት በተለይ በ72/73 ዓ.ም አንዳንድ የሰራዊቱ አመራሮች ፍፁም ፀረ-ዴሞክራሲያዊ የሆነ ተግባርን ይፈፅሙ ነበር ።ይህም ተራውን ተዋጊ በዱላ መቀጥቀጥና በገመድ የማሰር የሃሳብ ልዩነት ያለውን እንደ ሰላይ በመቁጠር እርምጃ የመውሰድ ኢሰብዓዊ ድርጊቶች ይፈፀሙ ነበር። እንደ ድርጅቱ የወቅቱ መሪ ይህን ለማስቆም ምን አድርገዋል?ምክንያቱም አንዳንድ ፀሃፊዎች ጣታቸውን ከድርጅቱ ወደ ተለያያችሁት የወቅቱ አመራሮች እየቀሰሩ ነውና።

**አቶ ግደይ፡-** እንደዚህ ዓይነቱ አሰራር በድርጅቱ ህግ የተከለከለ ነው ያስቀጣልም፡፡ ማንኛውም ታጋይ የዚህ ዓይነት ጥፋት ሲታይ ለበላይ መሪዎች የማመልከት መብት አለው፡፡ በተለያዩ ወቅት የተለያዩ ዝንባሌዎች የታዩበት ሁኔታ አለ፡፡ በስፋት የታዩ ዝንባሌዎች እንደ ወታደርነትና መኮንነት የመሰሉትን በዘመቻ ለማረም የተሞከረበት ወቅት አለ፡፡ ይህን ዝንባሌ ስንመታ በፖለቲካ ዲፓርትመንት የነበሩትን የነመለስን ተክለሰውነት ማጠናከርና የሴራ ካድሬዎቻቸውን እንዲያስለጥኑበት እድል ከፈተ፡፡ በሰራዊት መሪዎች በተለያየ ወቅትና ቦታ የተደረጉትን ጥፋቶችን ለማወቅ አልችልም፣ በቀጥታ የዚህ ዓይነት ጥፋት ተፈጽሟል የሚል ሪፖርት ከደረሰኝ ግን በድርጅቱ ህግ መሰረት ቅጣት ወይም ተግሳጽ እንደምሰጥ አልጠራጠርም፡፡

**ጥላ፡-** በትግሉ ወቅት ኢህአፓ ያቀረበውን የህብረት(የትግል) ጥሪ ህወሓት ያላስተናገደበት መሰረታዊ ጉዳይ ምን ነበር? አንዳንዶች በሁለቱ ድርጅቶች መካከል የነበረው የትምክህትና የጥበት አመለካከት ችግር ነው ይላሉ።እርሶስ?

**አቶ ግደይ፡-** ኢህአፓ ሶስት ደረጃ ያለው የህብረት ጥሪ ነበረው 1ኛው በኮምኒስት ፓርቲ ለተደራጀ ስትራቴጅክ የሚሉት፣ 2ኛው ለህዝባዊ ዲምክራሲያዊ ስርዓት ምስረታ ለሚታገሉት ዲምክራሲያዊ ግንባር የሚሉት 3ኛው ደግሞ ዲሞራሲያዊ ጥያቄ አንስተው ለሚታገሉት የጋራ ትብብር የሚሉት፡፡ በህወሓት እምነት ለህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት የሚታገል በሁለትኛው የኢህአፓ መመዘኛ የምታገል ነኝ ሲል ኢህአፓ አልተቀበለውም ምክንያቱም ህወሓት የኮሚኒስት ፓርቲ አመራር የለውም በሚል፡፡ በተጨማሪም ኢህአፓ የብሄር ትግል የዲሞክራሲ ጥያቄ ቢሆንም የሰራተኛውን የጋራ ትግል ያደናቅፋል የሚል አመለካከት ነበረው፡፡ በአንጻሩ ህወሓት የብሄር ጥያቄ በአሁኑ ወቅት ጎልቶ የሚታይና ህዝቡንም በቀላሉ ሊያነሳሳ የሚችል ስለሆነ በሰራተኛው ፓርቲ እየተመራ የሰራተኛውን ትግል ሊያጎለብት ይችላል የሚል አመለካከት ስለነበረው የኢህአፓን አቋም እንደንቀት ስላየው የቀረበለትን ሶስተኛውን አማራጭ አልተቀበለውም፡፡ ህወሓት ሶስተኛውን አማራጭ አለመቀበሉ ስህተት ነበር፡፡ በመጨረሻም ሁለቱም ድርጅቶች የተለያዩት "የማንኛችን ሂደት ትክክል ስለመሆኑ ጊዜ ይፈርደናል" በሚል ለግጭት በር በከፈተ መንገድ ነበር፡፡ ሂደቱም ያሳየን ይህንኑ ነው፡፡

**ጥላ፡-** ከኤርትራ የወቅቱ ተዋጊዎች ከነበሩት ሻዕቢያ፣ጀብሃ ወዘተ ጋር ህወሓት መስርቶት የነበረው ግንኙነት የጌታና የሎሌ አይነት ነው ብለው የሚከራከሩ ፀሃፍት አሉ።የእርሶስ እምነት ምንድን ነው?

**አቶ ግደይ፡-** ይህ አቀራረብ ከእውነቱ በጣም የራቀ ነው፡፡ በአብዛኛው ከኤርትራ ድርጅቶች ጋር የነበረው ግንኙነት የግጭትና አለመስማማት ሂደት ነው፡፡ ይህን ስል ግን የተጋገዙበትና የተባበሩበት ሁኔታ አልነበረም ማለት አይደለም፡፡

**ጥላ፡-** ህወሓትን በመፍጠር ባካሄዱት ትግል ይፀፀታሉ ወይ?ተቆጭተውስ ያውቃሉ?

**አቶ ግደይ፡-** በወቅቱ በነበሩት አንገብጋቢና ዲሞክራሲያዊ ጥያቄዎች ተነስቼ የብሄርን ጭቆና ለመታገልና በዚያውም በኢትዮጵያ ለዲሞክራሲ ከሚታገሉት ሌሎች ኃይሎች ጋር ሆኖ ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመመስረት በሚል ዓላማ ህወሓትን መፍጠሬና መታገሌ አይጸጽተኝም:: የሚቆጨኝ ነገር ቢኖር ግን ይህን ታላቅ የህዝብ ትግል ተገቢውን አመራርና አሰራር ሳንሰጥ ቀርተን ተመልሶ ህዝቡን የሚጨቁንና አገሪቱንም ሊበታትን የሚችል ስርዓት መፍጠራችን ነው:: ይህ እንዳይሆን ምን ሊደረግ ይችል ነበር ለሚለው ሰፊ ጥናትና ውይይት የሚያስፈልግ ሲሆን በበኩሌ አጠር ባለ መንገድ የሚከተሉትን ዘርፎች ማየት ይቻላል፣ አንደኛ የድርጅት ውስጣዊ ዲሞክራሲያዊ አሰራርንና በህብረተሰቡ የሚመሰረተው ዲሞክራሲያዊ መዋቅር በሚመለከት፣ ሁለተኛ በኢትዮጵያ ደረጃ የሚደረገውን የጋራ ትግል ትኩረት መስጠትን በሚመለከት፣ ሶስተኛ ከሌሎች ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ጋር የሚፈጠረው አለመግባባት አፈታትን በሚመለከት ቀደም ተብሎ ግንዛቤ ሊወሰድ ይገባ ነበር እላለሁ::

**ጥላ፡-** በስደት በቆዩባቸው ሶስት አሰርት ዓመታት ያካሄዱት ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ምን ይመስላል?

**አቶ ግደይ፡-** ህወሓትን ለቅቄ የወጣሁት በ1987 ዓ.ም ነው:: ከወጣሁ ጀምሮ የህወሓትን የተሳሳተ መስመርና ኢ-ዲሞክራሲያዊ ተፈጥሮ እንዲሁም በህዝቡ ላይ የሚያደርሰውን ግፍና በደል በግልም ሆነ በመደራጀት እየታገልኩ ነው:: ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ የትግራይ ዲሞክራሲያዊ ትብብር ትዴት (Tigray Alliance for National Democracy TAND) ከሚባለው ድርጅት ጋር ተሰልፌ የትግራይ ህዝብ ያለውን ስርዓት ከሌሎች የኢትዮጵያ ህዝቦች ጋር በመተባበር እንዲታገልና በጋራ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት እንዲመሰርት እየታገልኩ ነው:: በተጨማሪም ትግሉን ከሌሎች ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ጋር በማስተባበርና ሌሎችም ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች እንዲተባበሩና በጋራ እንዲታገሉ በማድረግ ትዴት የበኩሉን አስተዋጾ በማድረግ ላይ ነው::

**ጥላ፡-** በስደት የሚገኘው ህዝብ በተቃዋሚ ሃይሎች የእርስ በርስ መጠላለፍ ፈጣን ለውጥ ባለማየቱ ተስፋ የመቁረጥ ነገር ይስተዋልበታል።መፍትሄው ምንድን ነው ይላሉ?

**አቶ ግደይ፡-** እርግጥ የድርጅቶች እርስ



በርስ መጠላለፍና የአመራር ድክመት መታየቱ የህዝቡን የትግል ስሜት እንዲዳከም እንዳደረገው አያከራክርም:: ለትግል የገፋፉን ሁኔታዎች ማለት የዲሞክራሲ እጦት፣ የፍትህ መጥፋት፣ በጠባብ ብሔራዊ እምነት የሚደረግ አድልዎና ግፍ፣ የኑሮ ችግር፣ ብኩንነት፣ጭቆና ወዘተ እስካሉ ድረስ ትግሉ አይቆምም:: ስለሆነም ተስፋ ቆርጦ ከትግል መሸሽ ሳይሆን ያለን አማራጭ ድክመታችንን አርመን በተሻለ መንገድ መታገል ብቻ ነው:: ለዚሁም ከስምንት ወር በፊት የተለያዩ ድርጅቶችን አሰባስቦ "የኢትዮጵያ ህዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ" በሚል ስም የተደራጀውና የትግል አማራጭና አቅጣጫ ይዞ የቀረበው ጥሩ አብነት ሊሆን ይችላል፣ የተጠቀሱትን የተቃዋሚ ኀይሎች ድክመት ያስወግዳል የሚል እምነትም አለኝ::

**ጥላ፡-** እንደገለፁት በቅርቡ የተቃዋሚውን ሃይል በአንድ ጥላ ስር የማሰባሰብ ከፍተኛ ስራ ላይ ተጠምዳችሁ የኢትዮጵያ ህዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ መስርታችሁዋል።እስካሁን የሸንጎው እንቅስቃሴ ምን ውጤት አስገኝቷል?

**አቶ ግደይ፡-** ሸንጎ ከተመሰረተ 8 ወር ገደማ ሆኖታል:: በዚህ ጊዜ ውስጥ ድርጅታዊ መዋቅርን መቅረጽና ማጠናከር፣ ሸንጎን ለማስተዋወቅ በተለያዩ ትልቅ ከተሞች ህዝባዊ ስብሰባዎች ማካሄድና በሚድያ መግለጫዎችን በመስጠት፣ ደጋፊ ኮሚቴዎችን በተለያዩ ከተሞች ወይም አገሮች ማቋቋም፣ ከሌሎች ዲሞክራሲያውያን ኀይሎች ጋር ትብብር እንዲፈጠር ጥረት በማድረግ ሌሎች 8 ድርጅቶች የሚሳተፉበት የጋራ የትብብር መድረክ በመፍጠርና በመሳተፍ፣ በዲፕሎማሲ ስራ በአሜሪካና አውሮጳ ለሚገኙ አንዳድ የመንግስታት መስሪያቤቶች ግኑኝነት በመፍጠር ዓላማውንና የኢትዮጵያን ሁኔት ማስረዳት፣ የመሳሰሉትን ሰርቷል:: ሰፋ ያለ መረጃ ለማግኘት የሸንጎን ድህርገጽ http://www.ethioshengo.org/ መመልከት ይቻላል::

**ጥላ፡-** ሸንጎው በአገር ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ ሃይሎችን የማካተት ዓላማ አለው ወይ?ያደረጋችሁት ጥሪ ነበር? ምላሹስ ምን ይመስላል?

**አቶ ግደይ፡-** የሸንጎ ዓላማ ሁሉም ለዲሞክራሲ የሚታገል ኀይል አገር ቤት ይሁን ውጭ፣ በትጥቅ ትግል ይሁን በሰላም የሚታገለውን ሁሉ በጋራ በመቆም እንዲታገልና ያለውን ስርዓት አስወግዶ በዲሞክራሲያዊ ምርጫ ስልጣን ለህዝብ የሚሸጋገርበት ሁኔታ እንዲፈጠር መስራት ነው:: ስለሆነም አሉ የተባሉትን ታጋይ ኃይሎች ለማገናኘት ሞክሯል:: አገር ቤት ካሉት ታጋዮች ጋር በግልጽ ሊደረግ የሚችል ግንኙነት አሁን ያለው ሁኔታ አያመችም:: ትግሎቻችንን ግን ማቀናጀት እንችላለን:: ዋናው የትግል ሜዳ በአገር ውስጥ መሆኑን እንገነዘባለን:: አገር ቤት ያለው ስርአቱን ፊት ለፊት በመጋፈጥ መስዋዕትነትን ሲወስድ በውጭ ያለው ደግም ለትግሉ ደጋፊ የሆኑትን የዲፕሎማሲ፣ የገንዘብና የማቴሪያል ካስፈለገም የትጥቅ፣ የሚድያ፣ የምልመላ ድጋፍ ሊያደርግ ይችላል:: ሌላው ላስታስ የምወደው ሸንጎ ውስጥ ያሉ አንዳንድ ድርጅቶች የራሳቸው መዋቅር አገር ቤት እንዳላቸውም ጭምር ነው::

**ጥላ፡-** የሸንጎው ግብ ምንድን ነው?

**አቶ ግደይ፡-** የሸንጎው ዓላማዎችና ግብ የሚከተሉት ናቸው።

1ኛ/-በኢትዮጵያ ሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነትና ሉዓላዊነት፣እንዲሁም በአገሪቱ የግዛት አንድነት ላይ ግልጽና የማያወላውል እምነትና አቋም መያዝ፣

2ኛ/-የማንኛውንም ኢትዮጵያዊ ግለሰብ ዲሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶችን ማክበር፣በየድርጅቶች ውስጥና በምንሰባሰብበት የህብረት ማዕቀፍ ውስጥ ዲሞክራሲያዊ ግንኙነቶችንና አሠራሮችን በማስፈን መስራት፣

3ኛ/-በኢትዮጵያ ውስጥ የሕግ የበላይነት እንዲኖር ፀንቶ መታገል

4ኛ/-በኢትዮጵያ ሕዝብ መካከል ምንም አይነት አድሎ እንዳይኖር ሁሉም ዜጋ እኩል መሆኑን ማመንና በተግባርም ማረጋገጥ፣

5ኛ/-የህወሃት/ኢሕአዴግ መንግሥትና ሥርዓት የአፈናና የጭቆና

ሥርዓት በመሆኑ መለወጥና በዲሞክራሲያዊ አስተዳደር መተካት እንዳለበት ማመን፣

በተጠቀሱት ዓላማዎች ዲሞክራቲክ ኃይሎችን በማሰባሰብና በጋራ በመታገል ያለውን ስርዓት አስወግዶ ሁሉንም በዲሞክራሲያው መንገድ ሊያሳትፍ የሚችል የሽግግር መድረክ ተፈጥሮ ዲሞክራሲያዊ መድብላዊ ስርዓት እንዲፈጠር ነው፡፡

**ጥላ፡-** የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ሞት የሸንጎውን ግብ ከማሳካት አኳያ ምን ፋይዳ ይኖረዋል?

**አቶ ግደይ፡-** የመለስ ሞት በስርአቱ ላይ የአመለካከት ወይም የአሰራር ለውጥን አላመጣም፡፡ አሁን ያሉት መሪዎች ግን ስርዓቱን የመለስን ያህል ሊቆጣጠሩት አይችሉም፡፡ በውስጣቸውም የመከፋፈልና የስልጣን ፉኩቻ ፈጥሯል፡፡ ይህ ሁኔታ ለትግላችን አንዳንድ ቀዳዳዎችንና አመቺ ሁኔታዎችን ሊፈጥር ይችላል፡፡

**ጥላ፡-** በአሁኑ ወቅት ያለውን የኢትዮጵያ መንግስት ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ሸንጎው እንዴት ይገመግመዋል?

**አቶ ግደይ፡-** ይህንን በሚመለከት ሸንጎ “**የኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታና የሸንጎው የትግል አቅጣጫ** “ የሚል ሰፊ ጽሁፍ አውጥቷል ይህንን ማጣቀሻ በሚቀጥለው አድራሻ መመልከት ይቻላል፣ http://www.ethioshengo.org/files/ARCHIVE/Road_Map_A.pdf .

**ጥላ፡-** የኢትዮጵያ ህዝብ በኑሮ ውድነት በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ያለመስፈን በሰብዓዊ መብት ጥሰትና በግዳጅ የገዢው ፓርቲ አባልነት እየተማረረ ይገኛል።ግን በስርዓቱ ላይ የተደራጀ ተቃውሞን ሲያሰማ አይታይም።ችግሩ ምንና የማን ነው ይላሉ?

**አቶ ግደይ፡-** የህወሓት/ኢህአዴግ ስርአት አፋኝ በሆኑ አሰራሮችና ህጎች እንዲሁም ጨካኝ በሆኑ እርምጃዎች ተቃዋሚ ድርጅቶችና ህዝቡ እንዲዳከሙና እንዳይንቀሳቀሱ አድርጓቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ ከታሪክ እንደምንማረው ማንኛውም ጨቋኝ ስርአት ለአጭር ጊዜ እድሜውን ሊያራዝም ካልሆነ በስተቀር ጭቆናና ብሶት እስካለ ድረስ የህዝቡን መነሳሳትና መታገል ሊያግደውና ሊያስቀረው እንደማይችል ነው፡፡ ተቃዋሚ ኃይሉ ይህንን ለመመከት የሚያስችል ዘዴዎችን መፍጠር ግዴታ አለበት፡፡ 1 ለ 5 የሚለው የህወሓት/ኢህአደግ አሰራር ህዝቡን እንዳይላወስ ያደረገ አልቅስ ሲሉት እንዲያለቅስ፣ በግድ ምረጥ ሲሉት እንዲመርጣቸው፣ ሰላማዊ ሰልፍ ውጣ ሲሉት እንዲወጣ፣ ወዘተ አድርጎታል፡፡ የህዋሱ መሪ ካድሬዎች በጥቅም የተደለሉ አብዛኞቹ በመንግስት መስሪያ ቤቶችና ፕሮጀክቶች የሚሰሩ ናቸው፡፡ የተቀሩት አባሎች ደግሞ ከስራ እንዳይባረሩ ወይም ተመሳሳይ ጥቅም እንዳይነፈጉ ወይም እርምጃ እንዳይወሰድባቸው ፈርተው አጎንብሰው ያገለግላሉ ወይም ይኖራሉ፡፡ ተቃዋሚው ይህንን ህዋስ ማፍረስ አለበት።ለነገሩ ህዝቡም ብሶቱ እየጨመረ ሲሄድ ራሱ እያፈረሰው ይመጣል፡፡

**ጥላ፡-** በስርዓት ለውጡ ላይ የህዝብና የተቃዋሚ ፓርቲዎች ሚና ምን ይሆናል?

**አቶ ግደይ፡-** ተቃዋሚ ፓርቲዎች ህዝቡን ትክክለኛና ወቅታዊ አመራር በመስጠትና በማደራጀት ሲታገሉ ህዝቡም ለጥሪያቸው ተገቢውን ምላሽ በመስጠት በትግሉ መሳተፍን ይጠይቃል፡፡መታገል ሲባል በጉልበት፣ በገንዘብ፣ በንብረት፣ በሂወት፣ በችሎታ መሳተፍን የመሳስሉ ናቸው፡፡ በትግል ፓርቲና ህዝብ ተብሎ ተለያይቶ የሚሄድ ነገር አይደለም ሁለቱም አስፈላጊዎችና ተጣምረው መጓዝ አለባቸው፡፡

**ጥላ፡-** የሚዲያውስ?

**አቶ ግደይ፡-** ሚድያ ያለውን እውነታ ለህዝብ በማቅረብ የስርአቱን ምንነትና የአገሩን ሁኔታ እንዲያውቅ አገሩንና ጥቅሙን እንዲጠብቅ የሚያስችል አካል ነው፡፡ ጨቋኝ ስርአቶች በቅድሚያ የሚቆጣጠሩትና የሚያፍኑት ነጻ ሚድያን ነው፡፡ ከዚህም አልፈው የውሸት ፕሮፖጋንዳ ለማሰራጨት ይጠቀሙበታል፡፡ በኢትዮጵያ ያለውም ሁኔታ ይኸው ነው፡፡ ነጻ ሆነው ሊሰሩ የሚችሉ ሚድያ በውጭ ያሉት ናቸው፡፡ ህዝባችን ያለውን ያገራችን ሃቅና ሁኔታ በማቅረብ ህዝቡ እንዲማርና እንዲያውቅ በማድረግ ያለውን ስርዓት እንዲታገል የማድረግ ሃላፊነት አለባቸው፡፡

**ጥላ፡-** አቶ ግደይ ዘርዓፅዮን ስለሰጡን ማብራሪያ በአንባብያን ስም ከልብ እናመሰግናለን።

**አቶ ግደይ፡-** እኔም እድሉን ስለሰጣችሁኝ አመሰግናለሁ።በርቱ።

# የደም መንግሥት!

**Abba Haile Georgis Dinkneh/ Wetzlar**

በመጽሐፍ ቅዱስ ከ40 ጊዜ በላይ ስሟ የተጠቀሰላትና በዕቅፏ ከ85 በላይ ልዩ ልዩ ቋንቋ ተናጋሪ ብሔረሰቦችና ከ80 ሚሊዮን በላይ የሕዝብ ብዛት እንዳለባት የሚነገርላት ኢትዮጵያ ከዛሬ 6400 ዘመናት በፊት ጀምሮ የሰው ልጆች እንደሰፈሩባት በታሪክ መዛግብት የሚታወቀ ነው።

በተለይም በዓለም ሕዝቦች እጅ በሚገኘው መጽሐፍ ቅዱስ እንደተጠቀሰው በሥልጣኔና በንግድ ዘርፍ በብልጽግናና በመንግሥትነት ደረጃ ከታወቀች ሦስት ሺህ ዘመናትን አስቆጥራለች። ለዚህም ማስረጃ በ1ኛ ነገሥት 10:1 እና በ2ኛ ዜና መዋዕል9:1 ላይ ያለው ነው።

ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ የተረጋጋ ሰላም የሰፈነባትና የነፃነት ምድር መሆኗ በዓለም ዙሪያ ስለታወቀ ከባህር ማዶ ያሉ ልዩ ልዩ ሕዝቦችና ነገዶች ችግር በደረሰባቸው ጊዜ መሸሻቸውና መጠጊያቸው ኢትዮጵያ ነበረች።

ለምሳሌ ቀደም ባሉት ዘመናት በሃይማኖትና በባሕል የሚመስሉን ቤተ እስራኤሎች ሀገራችው በተለያየ ጠላት ስትወረር ነፍሳቸውን ለማትረፍ የግብጽንና የሱዳንን በረሃ አቋርጠው የሚመጡት ወደዚች ምድር እደነበር የታሪክ ጽሑፎች ብቻ ሳይሆኑ የትውልዳቸው ርዝራዥ የአካል ምስክር ነው።

እንዲሁም በ5ኛው መቶ ክ/ዘመን በታናሽ እስያና አካባቢው በጣኦት አምላኪዎች እንደ ባይተዋር ተቆጥረው ነፃነታቸውን ተገፍፈው ሥቃይ በበዛባቸው ጊዜ ከእሳትና ከሰይፍ ስለት አምልጠው የመጡ ክርስቲያኖችን በደስታ ተቀብላ ማረፊያ ቦታና መካነ አምልኮ ለመስጠቷ የነ አቡነ አረጋዊ ዘደብረዳሞ ገድላቸው ፣ አጽማችውና ገዳማቸው ሕያው ምስክር ነው።

በ7ኛው መቶ ክ/ዘመንም በመካከለኛው ምሥራቅ የእስልምና ሃይማኖት ሲመሠረት በተፈጠረው አለመግባባትና በተከሰትው ጦርነት ሀገራቸው በደም ስትነከር አይተው ተስፋ የቆረጡ መሐመዳውያን ነፍሳቸውን ለማትረፍ አማራጫቸው ኢትዮጵያ ብቻ መሆኗን ተረድተው ቀይ ባሕርን ተሻግረው ሲመጡ በሯን ከፍታ የተቀበለችና ነፍሳቸውን ያተረፉባት የክፉ ቀን ባለውለታችው መሆኗን ራሳቸው አፋቸውን ሞልተው የሚመሰክሩበት ጉዳይ ነው።

እንግዲህ ይህ ሁሉ የሚያሳየው ሀገሪቱ በቋንቋ ፣ በዘርና በቀለም ልዩነት የማታምን ስብእናን ብቻ መለኪያ ያደረገች ሀገር በመሆኗ ነው። በአጠቃላይ ኢትዮጵያ የሰላምና የነፃነት ፣ አምባ የሁሉም ነገድ ስብስብ የብሔረሰቦች መገኛ ስትሆን ሕዝቦቿም ቋንቋና ዘር ባህልና ሃይማኖት እንቅፋት ሳይሆንባቸው ወንዝ ሳይገድባቸው በመላ ሀገሪቱ ተስማምተው

ተቻችለው ተዛዝነው ተፋቅረው በጋብቻ ተቀላቅለው ተዋልደው ተዋሕደው በአንዲት ቋት ሰፍረው በአንድ ሕገመንግሥት ታስረው የኖሩባት ሀገር ናት።

መሪዎቿም በኢትዮጵያዊነት እንጂ በጐሣ የታሰረ መንፈስ ስለሌላቸው ዘርና ጐሣን ሳይሆን አንዲት ኢትዮጵያን ብቻ ሰብከው ብሔራዊ አንድነትን በሕዝቡ ልቦና ስለው አልፈዋል። ሀገሪቱንም ዳር ድንበሯን አስከብረው ክብሯን አስጠብቀው በሥልጣኔና በኪነጥበብ አስውበው ፊደል ቀርፀው የዘመን መቁጠሪያ ቀምረው የማንም ጥገኛ እንዳትሆን የብዙ ሀብት ባለቤት አድርገዋት አልፈዋል። ይህ እስከ 1983 ዓ.ም. ድረስ ያለው የትላንት ታሪክ ነው።

ይህቺ ከላይ ብዙ የተነገረላትና የተዘመረላት ኢትዮጵያ በ1983 ዓ.ም. የአሁኑ ገዥ መንግሥት ሥልጣን ላይ ከተቀመጠበት ጊዜ አንስቶ እስከ አሁን ባለው የ21 ዓመት ጉዞ ውስጥ ብሔራዊ አንድነቷ ፈርሶ ሰላሟ ደፍርሶ ታሪኳ ተፋልሶ ድንበሯ ተቆራርሶ ክብሯ ተጥሶ የታየበት አሳፋሪ ዘመን ነው።

የአሁኑ ገዥ መንግሥት የኢትዮጵያን ሕዝቦች ዳር እስከ ዳር እንደ ባቢሎን ሰዎች ከመግባባት ወደ አለመግባባት ፣ ከመፋቀር ወደ መቃቃር ፣ ከመከባበር ወደመናቆር ፣ ከአንድነት ወደ ልዩነትና ከኢትዮጵያዊ ህብረት ወደ ክልላዊ ስሜት እንዲያዘነብሉ ያደረገ የጥፋት መንግሥት ነው።

ይህ መንግሥት ቀደም ያሉት ታሪካዊና ወርቃማ ዘመናት በትውልዱ ዘንድ እንዲጠሉ ለማድረግ አንዱን ጨቋኝ ሌላውን ተጨቋኝ በማስመሰል ጥላቻን የሰበከ ፍቅርን ያቀዘቀዘ ብሔርን ከብሔር ጎሳን ከጎሳ በማናከስ ጥንት ተጋብቶና ተዋልዶ በሥጋና በደም የተሳሰረውን ሕዝብ በደም ያፋታና ደም ያቃባ ሐሳዊ መሲህ መንግሥት ነው። ለምሳሌ ጥቂቶቹን እንኳ ብንጠቅስ በደቡብ የጉጂና የደራሳን (ጌድኦን) ብሔረሰብ ፣ የኮንሶንና የቦረናን ብሔረሰቦች ፣ በወለጋ የኦሮሞን ሕዝብ ከአማራና ከጉሙዝ ብሔረሰብ ፣ የጋምቤላንም ሕዝቦች እርስ በእርሳቸው በማጋጨት በሺህ የሚቆጠር ሕዝብ ያስጨረሰ የደም መንግሥት ነው።

በ1997 ዓመተ ምሕረትም በተደረገው ብሔራዊ ምርጫ ሰበብ ባሳየው አምባገነናዊነት በአዲስ አበባና በሌሎች ከተሞች ድምፃችን ይከበር በሚሉ ንጹሐን ዜጎች ላይ በወሰደው እርምጃ የፈሰሰው ደም እስከ አሁን ድረስ ከተመልካች ኅሊና ውስጥ አልደረቀም። በሃይማኖትም ይኸው መንግሥት ሥልጣን ላይ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ በአሰቦት ገዳም መነኮሳትና በአካባቢው ሕዝበ ክርስቲያን ላይ የደረሰው አሰቃቂ ጭፍጨፋና እንዲሁም በአርባምንጭ ከተማ የኦርቶዶክስና የፕሮቴስታንት አማኞችን በማጋጨት የፈሰሰው ደም ፣ በጂማና በኢሊባቦር በስልጤና በጋሙጎፋ ክርስቲያኖችና አብያተክርስቲያናት ላይ የደረሰው ዘግናኝ ጭፍጨፋ በዓይን ላየው ሁሉ መፈጠሩን የሚጠላበት ክስተት ነው።

በዚሁ በጅማ ባለፈው ዓምት አካባቢ ከ40 በላይ የፕሮተስታንት ቤተክርስቲያኖች እና ንብረቶች ወድመዋል። በአጠቃላይ ይህ መንግሥት ሙስሊሙ ከኦርቶዶክሱ ኦርቶዶክሱ ከፕሮቴስታንቱ ተፋቅሮና ተቻችሎ እንዳይኖር አንዱን በአንዱን ላይ እያነሳሳ የሃይማኖት አቋማት ሲቃጠሉ ዳር ቆሞ እሳት መሞቅ የሚፈልግ መንግሥት ነው።

የሃይማኖት ተቋማት አልጋጭ ሲሉትም እርስ በእርሳቸው ማለትም ኦርቶዶክሱን ከኦርቶዶክስ ፣ ፕሮቴስታንቱን ከፕሮቴስታንቱ ፣ ሙስሊሙን ከሙስሊሙ እያተራመሰ የሃይማኖት ተቋማት ሰላም እንዳያገኙ እያደረገ ይገኛል። ከዚህም አልፎ ተርፎ ከ1500 ዘመን በላይ ተከብሮ የቆየውን የዋልድባን ገዳም እያፈረሰ በውስጡ የሚኖሩ መነኮሳትንም እያሳደደ ይገኛል። በዚህ ገዳም ብዙ አባቶች ከዓለማዊ ፍላጎትና ከእህል ተቆጥበው ቅጠላቅጠልና ፍራፍሬ ብቻ እየተመገቡ ቤት ሳይኖራቸው በዋሻና በዛፍ ሥር ተጠልለው ስለ አገር ብቻ ሳይሆን ስለ መላው ዓለም የሚጸልዩ አባቶች ያሉበት ገዳም ነው። በከተማ የደሀ ጎጆ እያፈረሰ በገዳም የአባቶችን ዋሻ እያረሰ መነኮሳቱን እያሳደደ በእጁ የገቡትን አስሮ እያሰቃየና እየገደለ ይገኛል። ገዳማትንም ያለ ቅርስ ትውልዱን ያለውርስ እያስቀረ ነው።

ስለዚህ ኢትዮጵያዊ የሆንህ አንባቢ ሆይ! ይህ ሁኔታ በዚህ ከቀጠለ በኢትዮጵያ ውስጥ ታሪክም ቅርስም ሕዝብም ሃይማኖትም ተሚጥተው ያልቃሉና የኢትዮጵያን ዕጣ ፈንታ እንደ ሶቬት ይሆናልና ለሕዝብህ ፣ ለወገንህና ለሀገርህ ስትል አጥልቀህ አስብ አጥብቀህ ጸልይ እልሃለሁ። የሰላም ባለቤት የሰላም አለቃ የሰላም ንጉሥ ኢየሱስ ክርስቶስ የጠፋውን ሰላም ይመልስልን! አሜን!

# ድምፅ አልባው አመፅ

**Here Fekru/Heppenheim**

ከሰማኒያ ሚሊዮን በላይ ህዝብ የሚኖርባት የብዙ ብሔሮችና ብሔረሰቦች መገኛ የብዙ ዓመት ታሪክ ያላት ሀገራችን ዜጎች በድህነት የሚማቅቁት ሳያንሳቸው ነፃነታቸውን ተነፍገው በሃገራቸው ላይ እንደ ሁለተኛ ዜጋ ተቆጥረው እርስ በእርሳቸው ባለመተማመን በጠላትነት አይን በማየት አንድን ብሔር ታማኝ ሌላውን ጠላት በማድረግ ህሊና የሌለውን በገንዘብ በመበደል በማሰቃየት በሃገሩ ላይ ነፃነትን አጥቶ በዝምታ ለመኖር ተገዷል።

የወያኔ ሚዲያ የመንግስት ፕሮፓጋንዳ የማስታወቂያና መዝናኛ ፕሮግራም አድርጎታል።በተለያየ ጊዜ የተለያየ ውሸት በመፍጠር እውነት በማስመሰል ድራማ እየሰራ አብዛሃኛውን ህዝብ በማደናገር ያልተሰራውን ተሰርቷል በማለት አጋኖ በማውራት አንድን ውሸት ደጋግሞ በመናገር ህዝቡ በወያኔ ሚዲያ በመማረር ሚዲያውን ማመንና መመልከት አቁሟል።

በአምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ጭቆና ውስጥ የሚኖረው ህዝብ ታፍኖ መብቱን ተነፍጎ የመሰብሰብ የመናገር ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብቱ ተገፎ በመማረር እየኖረ ነው።አብዛኛው ህዝብ በሚያየውና በሚሰማው ነገር ተማሮ ባገኘው አጋጣሚ ሃገሩን በመልቀቅ ነፃነት ወዳለበት ሃገር በመሄድ ድምፅን ያሰማል።አብዛኛው ህዝብ ዝምታን መርጦ የወያኔን ስራ በትዝብት ይመለከታል።ይሄ ዝምታ ግን አሁን ወደ ተግባር ሊለወጥ ይገባዋል።መብታችንን በትግላችን እናስከብር የኔ ጥሪ ነው! ሰላም ለኢትዮጵያ ይሁን።

# ማን ያውራ የነበረ ማን ያርዳ የቀበረ

**Zewdinesh Nigatu/Alsfeld**

በሀገራችን ለሚካሄደው ምርጫ ወያኔ መራሹ የምርጫ ቦርድ ከላይ እስከ ታች ካድሬዎቹን በማስቀመጥ ምርጫው ፍትሃዊና ዴሞክራሲያዊ እንዲሆን በመስራት ላይ ነኝ ሲል ተቃዋሚ ፓርቲዎች በበኩላቸው ያላቸውን ቅሬታ በማቅረብ እንወያይ ችግሮቻችንን እንፍታ

በሚል በተደጋጋሚ ለገዥው ፓርቲ ቢያሳስቡም ተቃዋሚዎች ለአካባቢ ምርጫ ትኩረት አይሰጡም ።ለሚያቀርቡት ጥያቄም ማስረጃ የላቸውም በማለት ምርጫ ቦርድ ሲገልፅ ለእኔ ይገርመኛል።ለመሆኑ የኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ የህዝብ ግንኙነት ሃላፊ ወ/ሮ የሺ ፈቃደ ማናቸው?ገለልተኛ ናቸውን?

በኢትዮጵያ አቆጣጠር በ1982 ዓ.ም በሰሜን ወሎ አስተዳደር ከዋድላ ደላንታ አካባቢ ወያኔን የተቀላቀሉ በተለያዩ ወረዳዎች በኢህዴን/የአሁኑ ብአዴን/ክፍለ-ህዝብነት በሁዋላም በብአዴን ካድሬነት በሰሜን ሸዋ ዞን ታች ቤት ወረዳ፤በደብረ ብርሃን ከተማ አስተዳደር ሲያገለግሉ ከቆዩ በሁዋላ በጎጠኛው የብአዴን አመራር ድጋፍ በደቡብ ወሎ ዞን ጢጣ በተከፈተው የወያኔ አዳሪ ትምህርት ቤት 12ኛ ክፍልን እንዳጠናቀቁ ለ2 ዓመት ከቆዩ በሁዋላ በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ የመጀመሪያ ዲግሪ በመማር ላይ እያሉ በ1997 ዓ.ም ምርጫ በደብረብርሃን ከተማ አስተዳደር ብአዴን ኢህአዴግን በመወከል ለአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ለምርጫ ቀርበው በቅንጅት የተሸነፉ ሲሆን ተመርቀው ሲወጡ የሰሜን ሸዋ ዞን ሴቶች ጉዳይ መምሪያ ሃላፊ ሆነው ተሹመው ነበር።ወያኔ የአዲስ አበባን የህዝብ ተቃውሞ ይመክታሉ ያላቸውን ካድሬዎቹን ከክልሎች እየመለመለ ሲያስገባ እሳቸውም የተልዕኮው አካል በመሆን ለተወሰነ ጊዜ በኢህአዴግ ፅ/ቤት ከሰሩ በሁዋላ ታጋይ የሺ ፈቃደ በኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ የህዝብ ግንኙነት ሃላፊ በመሆን ወያኔ ማንንም ሳይፈራ ሾማቸው።የተሰጣቸውን ተልዕኮም በመፈፀም ላይ ይገኛሉ።

ለመሆኑ በየትኛው ፀበል ተጠምቀው ነው ነፃና ገለልተኛ የሆኑት?ለ22 ዓመታት ሲመሩት የነበረውን ህዝብ ትንሽ እንኳንሳይፈራ ወያኔ

አይኔን ግንባር ያድርገው ምርጫ ቦርድ ነፃና ገለልተኛ ነው ሲል የምርጫ ቦርዱም ሃላፊ ይህንኑ ደገሙት።የ1997 ዓ.ም የዕጩ መመዝገቢያ ሰነድ የለምን?ለተቃዋሚዎች ማስረጃቸው ከማንም በላይ ህዝቡ ነው።ህዝብን ማታለል አይቻልም ሃቅን መደበቅም አይቻልም።ህዝቡ ያሸንፋል።በአገራችን ነፃ ፍትሃዊና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ስርዓት ለማስፈን በአንድነት ጠንክረን በመታገል ወያኔ ኢህአዴግን ከህዝቡ ጫንቃ ላይ ልናነሳው ይገባል።

# የኢትዮጵያ ሴቶች የአረብ አገር ሰቆቃ

**Sosina Kebede Alemayehu/ Würzburg**

ኢትዮጵያዊያት እህቶቻችን በአረብ አገር የሚደርስባቸው ስቃይና መከራ ለአገሪቱ ዜጎች በስደት መንከራተት በቂ ማሳያ ነው።በዚህ ዘመንም መንግስት ከሌላት ሶማሊያ በበዛ ሁኔታ ህዝባችን በገዛ መንግስቱ በሚደርስበት በደል በመሰደድ ግንባር ቀደም ሆኗል።

በተለይም ባለፉት 20 ዓመታት በግፈኛው የወያኔ መንግስት ህዝባችን በደረሰበት በደል ምክንያት የስደት ህይወትን መርጦ በሃይማኖትና በባህል ወደማይመስሏቸው አረብ አገራት በመሰደድ ስብእናቸውን ሸጠው ለመተዳደር ተገደዋል።በተለይ እህቶቻችን በቤት ሰራተኛነት በሚሰሩባቸው አረብ አገራት የመገረፍ የመደፈር ለአካል ጉዳት የመዳረግና የግድያ ወንጀል ሰለባዎችም በመሆን ላይ ይገኛሉ።ይባስ ብሎ በየመን በኩዌት በባህሬን በዱባይ በሳዉዲ አረቢያ በኳታር በእሳት እየተቃጠሉ በር ተቆልፎባቸው በገመድ እየታሰሩና ከፎቅ እየተወረወሩ የፈላ ውሃና ዘይት እየተደፋባቸው ሳይቀር እየተሰቃዩ ናቸው።በቅርቡ በኩዌት ሞታ የተገኘችውን ወጣት ታሪክም hethiomedia.com መመልከት በቂ ማስረጃ ነው፡

ስለዚህ ተዋርዶ ያዋረደንን ስርዓት በዴሞክራሲያዊው ለመተካት ያለንን እናበርክት ጥሪዬ ነው! ሰላም ለአገራችን!

# አሁንም ምርጫው ኢ-ፍትሃዊ ይሆናል!

**Hanna Nigusse/Meseret Kebede – Arnsberg**

የወያኔ ኢህአዴግ ስርዓት ሰሞኑን ለአካባቢና ለማሟያ ምርጫ በሚል ቀልድ ላይ ተጠምዷል።የፌታችን ሚያዝያ ለሚካሄደው ምርጫም ህዝቡን የመራጭነት መታወቂያ እንዲወስድ በማስገደድ ላይ ነው።ግን ይኸኛውም ምርጫ እንደባለፉት ምርጫዎች ሁሉ ገና ከጅምሩ ገዥዉ ፓርቲ 99ነጥብ 9 በመቶ እንደሚያሸንፍበት ሳይታለም የተፈታ ነው።

ወያኔ አንድ ለአምስት(one to five)በሚለው የስለላ መዋቅሩ ህዝቡን እርስ በራሱ እያሰለለው በምርጫው ሳይሆን ተገዶ እንዲመርጠው ከወዲሁ አዘጋጅቶታል።

ለስሙ 33 ፓርቲዎች ለውድድሩ ተመዝግበዋል ቢባልም አብዛኞቹ ኢህአዴግ የፈጠራቸውና የራሱ አቀንቃኞች ወይም በብሔር የተደራጁ ጠባብ ሃይሎች ናቸው። ዋነኞቹማ ምርጫው ፍትሃዊ ስርዓትን የሚከተል አሰራር ስለሌለው በምርጫው ለመሳተፍ ከመወሰናችን በፊት ገዥው ፓርቲ የስለላ መዋቅሩን ያፍርስ እያሉ ነው።

ስለዚህ ዋነኞቹ ተቃዋሚ ሃይሎች በማይሳተፉበት ሁኔታ ምርጫ አለ ማለት አሁንም ምርጫው ኢ-ፍትሃዊ እንደሚሆን ማሳያ ነው።ምርጫው ሳይካሄድ ሊጋሽ አገራትና የኢትዮጵያ ወዳጆች የምርጫው ስርዓት እንዲስተካከል የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ እለምናለሁ።

# በአሁኑ ወቅት የህወሃት / ኢህአዴግ/ አባል ያልሆነ በኢትዮጵያ የመኖር መብት የለውም፡፡

**Debebe Kebede / Goch**

ስለአገራችን ኢትዮጵያ ያልተዳፈ ያልተነገረ በህዝቦቹም ላይ ያልተፈጸመ በደልና ግፍ የለም እየተፈጸመም ነው፡፡ ወያኔዎች የኢትዩጵያን ህዝብ በአንድ ብረት /አጥር/ ውስጥ ተዘግቶበት እንደሚኖር አንበሳ አድርገውታል። ከነሱ ጩኸትና የውሸት ፕሮፓጋንዳ ሌላ እንዳይሰማና እንዳያይ አድርገው የውጭ ሚዲያዎችን ሁሉ በመዝጋት አደንቁረው ረግጠው እየገዙት ይገኛሉ፡፡

የእስከአሁኑም ግፍ ጭቆናና በደል አልበቃ ብሏቸው በነሱ አቀማመር ቀጣይዎቹንም አሰርት አመታት ከአንድ ብሄር በተውጣጣው በህውሃት ቅኝ ግዛት ስር የሚቆይበትን ሥልት እያመቻቹ ነው፡፡

እንደሚታወቀው ህወሃት/ኢሕአዴግ ግን የሚያስጨንቀውና የሚያራውጠው ወይም እንቅልፍ የሚነሳው የሃገርና የህዝብ ጉዳይ ሳይሆን የስልጣን ዘመኑን የሚያራዝምበትን ስትራቴጂዎችን መቀየስ በመሆኑ ለዚህም እኩይ አላማውን ለማሳካት ይረዳው ዘንድ በአሁኑ ወቅት የትኛውም የኢትዩጵያ ህዝብ ሳይወድ በግድ ህወሃት/ኢሕአዴግን እንዲደግፍና አባል ማድረግ እንደዋነኛ አማራጭ ወስዶ ህዝብን በመሰብሰብና በማስጨነቅ ላይ ይገኛል፡፡

በመሆኑም ካድሬዎቹን ከከተማ እስከ ገጠር መንደሮች በማሰማራት ህዝብን በሃይል በማስማፈራራትና በማሰር እንዲያውም በገንዘብ በማታለል በአባልነት እንዲፈርም እያደረገ ነው፡፡

አባል ያልሆነውን ሠራተኛውን ከሥራ በማባረር ገበሬውንም መሬቱን በመንጠቅ ህዝቡን ለረሃብና ለስደት እንዲጋለጥ አድርጐታል፡፡

የመንግስት ሰራተኛውም ሆነ ገበሬው በስብሰባ ተወጥሮ የሥራ ጊዜውን በከንቱ እያባከነ የነሱን ጩኸት እንዲያዳምጥና በነሱ ሰይጣናዊ መንፈስ እንዲጠመቅ ወያኔ ሃይል በመጠቀም ላይ ሲሆን የአገሪቱንም ኢኮኖሚ ለራሱ አላማ ማስፈጸሚያ እያዋለው ይገኛል፡፡

እንግዲህ ይህ ሁሉ ሸርጉድ ለአንድ አምባገነን ፓርቲ ህዝብን አፍኖ ለሚገዛ ለሚገድልና በሰው ደም ለሚቀልድ እድሜ ማራዘሚያ ተብሎ ለስብሰባ ወጪ ማድረግ አባል ለሆነ በሚል በብዙ ሚሊዩን ብር የሚቆጠር አበልና ትራንስፓርት በመከፋፈል የመንግስት ገንዘብ ማባከን ምን ያክል በሃገርና በህዝብ ላይ መቀለድ ነው፡፡

በአጠቃላይ በተደጋጋሚ እንደተገለጸው የሃገር ነጻነት ሊመጣ የሚችለው በአንድነት በመተባበር ሲሆን ለዚህም ሁሉም የተቃዋሚ ፓርቲዎች አንድ የሆነ ወያኔን የማስወገድ አላማና ለአንድ አገር ለአንድ ህዝብ ነጻነት የሚታገሉ መሆናቸውን አምነው ትግሉን ሲቀላቀሉ ብቻ ነው፡፡ለዚህ እንተባበር። አንድነት ሃይል ነው!

# መፍረሱ አይቀርም

**Alem Kebede Welde/Germany**

ኢትዮጵያ ሀገራችን በአሁኑ ሰዓት ወሳኝ አስተዋይ ቆራጥ አመራር ያለው ዜጋ ያስፈልጋታል።በመፈራረስ ላይ ያለው ዘረኛና አምባገነን ስርዓት እያረጀና በራሱ ጊዜ መውደቂያው እየተቃረበ ስለሆነ ሃገሪቷን ከመበታተን እና አዘቅት ውስጥ ከሚጥል ሁኔታ ለመታደግ ወሳኝና ቁርጠኛ ልጆች ያስፈልጓታል።

ይህ ትውልድም ያረጀውን ስርዓት ጥንቃቄ በተሞላበት ትግል አስወግደን ሰላማዊ ስርዓት ለማምጣት ይህን ማድረግ የሚችል ዜጋ መፍጠር ይገባናል።

ያረጀውን ስርአት ለማስወገድ ህብረት ማድረግ ደግሞ የግድ ይለናል።የሚለው ቢኖረኝ ወገኔ እኔን ማለት ትተን እንደ አባቶቻችን ሃገሬን ቤቴን ማለቱን ትተን ጫካውን በማለት ወደ ውድቀት እየሄደች ያለችውን ሀገራችንን እናስባት እላለሁ።ይህ ጥሪዬ ለወገኔ ይድረስ።ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!

# የወያኔ አገርንና ህዝብን የመበታተን ተንኮላዊ ሴራ

**Genet Zewdie /Duisburg**

በሚሊዩን የሚቆጠሩ ዜጐች በየዘመኑ በህይወት መስዋእትነት ጠብቀው ያኖሩትን የኢትዮጵያን አንድነት ዛሬ ከጫካ የወጣው ስብሰብ /ወያኔ ከራሱ ጥቅምና በትእቢት መወጠር ሌላ አገር አንድነትና የሰው ልጆችን እኩልነት የማያውቅ ሰውን መግደልና ማሰርን

የተለመደ ባህሪው ያደረገ እብሪተኛ ነው፡፡

ዛሬ ወያኔ በአገርና በሕዝብ ላይ ነገ ሊድኑ የማይችሉ ብዙ ጠባሳዎችን እያጣለ ያለ ቢሆንም ሃገራችንን ከሁሉ በላይ እያሳሰባት ያለው ግን ወያኔ ገና ጫካ እያለ የደቀነባት አገርን የመገነጣጠል ስትራቴጂ ነው፡፡

ይህንንም አገርን የመገነጣጠል መሰሪ አላማው ሰሞኑን ከህወሃት /ኢሕአዴግ/ አንጋፋ መሪዎቹ ይፋ እየሆነ የመጣ ሲሆን በቅርቡ የስርዓቱ ቁንጮ ከሆኑት አንዱ በረከት ስምኦን /አረቢክ/ የሚባል ፓልቱክ ላይ ቀርቦ ቃለ ምልልስ ሲያደርግ እንደ ተከታተልነው መገንጠል ለሚፈልግ ጊዜው ሲደርስ መገንጠል መብቱ ነው ሲል ተደምጧል፡፡ ጊዜው ሲደርስ ማለቱ እንግዲህ ኢትዩጵያ በአሁኑ ወቅት ዘረኞቹ ህወሃቶች ፈላጭ ቆራጭ የእጅ መዳፍ ውስጥ ያለች በመሆኗ እነሱ እንደፈለጋቸው / እንዳመቻቸው/ የሚበጣጥሷት ወይም የሚቀጣጥሏት እንደ ሆነች እየነገሩን መሆኑ ነው፡፡

በዚህ መሰረት ወያኔዎች አላማቸው እንግዲህ አቅማቸው እስከፈቀደ ድረስ ተቃዋሚ ሃይሎችን አጥፍቶ ኢትዮጵያን እየዘረፈ መኖር ቢሆንም ይህ ካልተሳካና ተቃዋሚ ሃይሎች ወያኔ ላይ ጫና በማሳደር የወያኔን ስልጣን አደጋ ላይ ይወድቀል ብለው ከሰጉ እነሱ ትግራይን ተቆጣጥረው ሌላውን የኢትዮጵያ ክፍል በታትነው መሄድ ነው፡፡ እኛም ይህንን ተገንዝበን እነዚህን የሃገርና የህዝብ ቀንደኛ ጠላቶች ልንነቅላቸው ይገባል፡፡ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር

# ይብቃ በፍርሃት መኖር

**Sina Araya /Alsbach-Hähnlein**

***A People should not be afraid of his government, his government should be afraid of the people!!***

ይሄ አባባል የኔ ምኞት ነው ለሃገሬ ለኢትዩጵያ እንዲሆን የምመኘው አሁን ባለው መንግስት በሚያሳዝን ሁኔታ እውነታው የዚህ ተቃራኒ ስለሆነ እውነታው አሳዛኝ ነው በፍርሃት የሚኖር ህዝብ ያሠበውን የሚፈልገው መናገር ያየውን መጥፎ ነገር መንቀፍ ያለ ኢሕአዴግ ፓርቲ አባልነት የፈለገውን ስራም ሆነም ትምህርት ማግኘት የማይችልበት አንገቱን ደፍቶ እያየ እንዳላየ እየሠማ እንዳልሠማ እንዲኖር በመሣርያ ሃይል የተገደደበት ጉልበቱ እየተበዘበዘ በሱ የላብ ዋጋ ሌላው ሲዝናና ሲጨፍር የሚያይበት፡፡ በትምህርትና በችሎታ ወይም በልምድ ሣይሆን በኢሕአዴግ አባልነት ስልጣንም ሆነ እድገት የሚገኝበት ለመንግስት ያላጐበደደ በልቶ የማያድርበት ...ኧረ ስንቱ... የመረረውና ተቃውሞውን ያሳየ የሚታሠርበት የሚገረፍበት እና እስከ ሕይወቱ ማጣት የሚደርስበት... በእውነት የሚያሳዝን.. ሕዝብ

እናም ወገኔ ምኞት ብቻ አይደለም እንነሳ እንታገል እንጩህ እኛ ከዚህ ፍርሃት ውስጥ አምልጠን እዚህ የደረስን ዝም አንበል ለአለም የኢሕአዴግን አንባገነንነት እናሣውቅ እንታገል ህዝባችን ያለ ፍርሃት የሚኖርበት ቀን ቅርብ ነውና። ድልና ነጻነት ለኢትዩጵያ ህዝብ፡፡

# አይ ሃገሬ

**Asnakch Telahun / Würzburg**

ኢትዮጵያ ለም አገር ስለሆነች በአመት ሶስት ጊዜ ሠብል ስለምታፈራ የዳቦ ቅርጫት እንዳልተባለች ሁሉ በኢህአዴግ ዘመን ህጻናትና እናቶች በረሃብ እየሞቱ ግባ መሬት ሲባሉ ግፈኛው ዘረኛው የኢህአዴግ መሪ የኢትዮጵያን ገበሬ ከእርሻቸው እያባረረ የእርሻ መሬቱን ለህንድና ለፓኪስታን በርካሽ ዋጋ በመሸጥ ገንዘቡን በግል ኪሱ ሲያስገባ የኢትዩጵያ ገበሬዎች በራሣቸው ሠብል የበላተኛ ተመልካች ሆነዋል፡፡

ይህ መንግስት አይቶ በቃኝ ማለት ስለማያቅ እንዲህ በደብረ ዘይት እንዲሁም በደቡብ የሚገኘውን መሬት እየቸበቸበው ነው፡፡ ስለዚህ ወያኔ መላውን ህዝብ አደጋ ውስጥ ከመክተቱ በፊት ሁላችንም ለጋራ ዓላማ በጋራ እንነሳ እላለሁ።በአገራችን እንደ ሁለተኛ ዜጋ መታየታችን እንዲቀር ዛሬ የበኩላችንን ለመወጣት እንዘጋጅ።

# ለወሳኙ ድል እንነሣ

**Aschalew Mengistu / Hückelhoven/**

እናት ሃገራችን ኢትዮጵያ ከመቸውም በበለጠ የችግር አረንቋ ውስጥ ወድቃ ትገኛለች፡፡ ጨቋኙ የወያኔ የግፍ አገዛዝ በሌላ መልኩ እየቀጠለ በሚገኝበት በዚህ በከፋ ችግር ወቅት የተሻሻለ መስተዳደር ይመጣል ብሎ መገመት እንደ ሞኝነት ያስቆጥራል፡፡

የድሮው ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ወያኔ የግፉ አገዛዝ ቁንጮ ወደ ማይመለስበት ዳግመኛ ዓለም ከተጓዘ በኋላ በምትካቸው የቀደሞው ም/ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ ተተክተው መንበረ ሥልጣን ይዘዋል። ግና ምን ያደርጋል ቃለ መሃላ ባደረጉ ማግስት ታማኝነታቸውን ለድርጅታቸው ሕ.ወ.ሃ.ትና ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ወይም ለባለቤታቸው ወ/ሮ አዜብ መስፍን ማስተዛዘኛ በሚመስል መልኩ የታላቁ መሪያችንን ፖሊሲን ስትራተጂ ሳይበረዝ ሳይከለስ እንደሚቀጥሉ በተግባር እንደሚተረጉሙ ባንደበታቸው ተደምጧል፡፡

እናት ሃገራችን የምትፈልገው የሥልጣን መሸጋሸግ ሳይሆን እውነተኛ ለሕዝብ የቆመ የሕዝብን መብት የሚያስጠብቅ ዲሞክራሲያዊ በሆነ መልኩ የሚመራ የሕግ የበላይነትን ተቀብሎ በፍትህ የሚያምን በሃይማኖት በጐሣ ከፋፍለህ ግዛ መንገድን የማያምንና የማይከተል ሲሆን ነው፡፡

ነገር ግን ሃገራችን ውስጥ ያለው ድራማ ረሃብ፣ ስቃይ ፣ ሰቆቃ ፣ ስደት ፣ እስራት ግድያ ወዘተ ሲሆኑ በአንጻሩ በጥቂት ቱባ የወያኔ ጀነራሎችና ለሆዳቸው ያደሩ አድር ባይ አፍቃሪ ወያኔዎች የምድር ገነታቸውን እያዩ ሲንደላቀቁ ቢታዩም አገራችንን ከገባችበት ማጥ አረንቋና የሙስና ስልት በተባበረ የሕዝብ ክንድ እንደሚስተካከል ለአፍታም አንጠራጠርም፡፡

አሁን እየከፋ ያለው በሙስሊሙ ኢትዮጵያዊ ወንድሞቻችን ላይ እየደረሰ ያለው የሃይማኖት አፈናና የሙብት እረገጣ እጅጉን የሚያሳዝንና አመት የፍትህ ያለህ የሚያሰኝ የሰቆቃ ጩኸት ቃጭልና ደውል የሚያስደምጥ ይሆናል፡፡

በኦሮሞ ሕዝብ በአማራው፣ በኦጋዴን ሕዝቦች ላይ እየደረሰ ያለው የግፍ የበቀል እርምጃ ይህ ነው ተብሎ ሊገመት አይቻልም፡፡ አገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ ኢ-ዲሞክራሲያዊነት የፕሬስ አፈና ጋዜጠኞች በየቀኑ ወደ ዘብጥያ መወርወር፣ ትላልቅ እንድስትሪዎችና ሰፋፊ እርሻዎችን ለህዳሴው ልማት በሚል ሰበብ ለውጭ ባለሃብቶች እየተቸበቸበ ይገኛል ከዚያ የሚገኘው ገቢም ለጥቂት ቱባ የወያኔ ባለስልጣናት የግል ኮረጆ መሙያ እየሆነ ነው፡፡

እንግዲህ ወያኔ ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ በገዛ ሕዝቡ ላይ ይሕን ያህል በደል እየፈጸመ እያለ የኛስ ድርሻ ምን መሆን ይገባል?አማራጩ በተባበረ የኢትዮጵያ ልጆች ክንድ ትላንት በሞት እንዳለፈው መለስ ቀሪውን ድርጅቱን ህ.ወ.ሃ.ት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግን መቃብሩን ማዘጋጀት ይኖርብናል። ይህ ግብአት የሚፈፀመው ሁሉም ዜጋ ሲተባበር ነው በውጭ የሚገኝ ዲያስፖራ በአገር ውስጥ ያለ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በመደጋገፍ በመተባበር ለትጥቅ ትግል ለመዘጋጀት እናት ኢትዮጵያ ከገባችበት አረንቋ እናውጣት የሕዝብ ትግል ምንግዜም አሸናፊ ነው፡፡

እናት ሃገር ኢትዮጵያ ከወያኔ መንጋጋ ለማላቀቅ ወገብ አጥብቆ ሱሪን ባጭር ቆርጦ ከጀግና ተጋዳይ ነጻ አውጪ ብርቅዬ የኢትዮጵያ ጀግና ልጆች ጐን ተሰልፈን የመጨረሻውን የወያኔን ስርአት ማብቂያ ማብሰር ይጠበቅብናል፡፡የተባበረ የሕዝብ ክንድ አሸናፊ ነው፡፡"እግዚአብሄር ኢትዮጵያን ይጠብቅ"ቸር ይግጠመን!

# መንግስት ከእምነት ተቋማት ላይ እጁን ያንሳ

**Kidest Zelalem/Köln/**

ደጀ ሰላም እየተባለ የሚጠራውና ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲየን ነባራዊ ሁኔታ እየተከታተለ በሚከተለው ድረገጽ ላይ እየተነበበው በጥር 13,05,2005 /በ January 20,2013 "አንድ ጥምቀት፣ አንድ ሃይማኖት" የሚል ጥቅስ የያዙ ወጣቶች ታሰሩ ይላል፡፡ በማከልም ቅዱስ ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች በላከው መልእክቱ ምእራፍ 4 ቁጥር 5 ላይ ያለውን አንድ ጥምቀት ፣ አንድ ሃይማኖት እንዴትነት ሁኔታውን ሲያብራራ፡፡

ጥር 11/2005 ዓ.ም ታላቁን የጥምቀት በዓል ምክንያት በማድረግ ታቦተ ሕጉን ተከትለው በሞቀና በደመቀ ሃይማኖታዊ መንፈስ በማክበር ላይ እያሉ በፖሊስ የታሠሩት ስድስት ወጣቶች ሲሆኑ ጥቅሱ የተጻፈበትን ቆብ ይሸጡ የነበሩት ደግሞ ለብርሃናተ ዓለም ጴጥሮስ ወጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ት/ቤት ገቢ ለማስገኘት በሚል እንደሆነ ተገልጿል፡፡

መንግስት የሃይማኖት አክራሪነትን

እዋጋለሁ በሚለው እውቀት የጐደለው ተግባር አንድ ሃይማኖት የሚል ቃል የሚናገሩ ክርስቲያኖችን በሙሉ በማሳደድ ላይ ይገኛል፡፡ የመጽሃፍ ቅዱስ ሃይለ ቃል እና የቤተ ክርስቲያኒቱ መሠረተ እምነት የሆነውን ቃለ እግዚአብሄርን መናገር ማስተማርም ሆነ በጽሁፍ መያዝ ሌሎች እምነቶችን እንደመዋጋት ተደርጐ እንደሚቆጠር በመናገር በፖሊስ ጥብቅ ማዋከብና እንግልት የሚፈጽመው ኢሰብአዊ ድርጊት ተባብሶ እየቀጠለ ነው፡፡ ለዚህም መንግስት እነዚህን ስድስት ልጆች የያዘው በዚሁ ምክንያት መሆኑን በወቅቱ በቦታው የነበሩ እማኞች ገልጸዋል፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ ከነበሩ ቀደምት መንግሥታት ሁሉ በባሰና በከፋ መንግስት በቤተ ክርስቲያኒቱ የውስጥ ጉዳይ ረዥም እጁን አስገብቶ የሚያምሰው የፖለቲካው መዘውር በቅርቡ በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤያት ላይ ሳይቀር ባለሥልጣኖቹን በመላክ የሲኖዶሱ ተሰብሳቢ ለመሆን በመሞከር ላይ ነበር፡፡ እንደተመኘውም ሁለቱ ሲኖዶሶች እንደተለያዩ እንዲቀሩና እርቀ ሰላም እንዳይወርድ ሲኳትንለት የነበረው ዓላማም ተሳክቶለት እሱ የሚፈልገውን ፓትርያርክ ሊመርጥ ለሰርግ ሽርጉድ ማለቱን እንደሚቀጥልም የታመነ ነው፡፡

መንግሥት በአገሪቱ ቀደምት እምነቶች ላይ ያለውን አቋም ለካድሬዎቹ በተከታታይ ሥልጠና በመስጠት የሚያስጠናበት ሰፊ እንቅስቃሴ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ድረስ በቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ እና በሌሎች ኃላፊዎች ሲሰጥ የቆየው ሥልጠና ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እና እስልምና ላይ ያነጣጠረ ሲሆን ለረጅም ዓመታት አብረው በፍቅርና በሰላም ሲኖሩ የነበሩትን የኦርቶዶክ ክርስትናና የእስልምና እምነት ተከታዩችን እርስበርስ ለማናቆር መንግስት በነባር አገራዊ ቤተ እምነቶች ላይ እያስፋፋ የመጣው ጣልቃ ገብነትና ድንበሩን አልፎ የኦርቶዶክስና የእስልምና መሪዎችን በማሰር፣ ብሎም የተለያዩ እንግልቶችን በማድረግ እኩይ ተግባር እየሰራ እንደሆነ ተደጋግሞ መገለጡ ይታወቃል፡፡

ነገር ግን እኛ ኢትዮጵያውያን ዛሬ ታይቶ ነገ በሚጠፉ ጊዜያዊና ጥቅመኛ መንግስት መቼም ቢሆን መቼም ኢትዮጵያዊነት ማንነታችን ሊሸረሸር አይችልም፡፡

# የኢትዮጵያ ትንሳኤ አሁን ነው

**Birtukan Abebe / Würzburg**

ትግሉን ማፋፋም እንጂ የምን ማቆም አሁን ያለው በየቀበሌው ጀግናው መሪያችን የጀመረውን ልማት እንቀጥላለን በወሬ ብቻ የምትመራ ሃገር ውድ የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ ይህ የወያኔ መንግስት ከስሩ ነቅሎ ለመጣል አሁን ነው ሰአቱ። በአጋጣሚው ተጠቅመን ለነጻነት ለዛሬም ለቀጣይም የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ እስከ አሁን በግፉና በጭቆና ተገዛህ ከዚህ በኋላ በግፍ መገዛት ይቁም በአምባገነኑ መገዛት ይቁም፡፡

በአሁኑ ሰአት በሃገራችን ያለውን የዘር የባህልና የነጻነት ወረራ ለማቆም በአንድነነት ከመሰለፉ ሌላ ምን አማራጭ አለን?

ኢትዮጵያዊነት የአንድ ማህበረሰብ ወይመ ባህላዊነት መገለጫ ሳይሆን በኢትዮጵያ ምድር ለሚኖሩ ብሄረሰቦች ሁሉ ከብዙነታቸው በላይ አብሮነታቸውን ውህደታቸውን ገላጭ ክብርና ሞገሣቸው ከመሆኑም በላይ የአንድነታቸው የቃልኪዳን ማህደራቸው ነው፡፡በአሁኑ ሰአት እግዚአብሄርም እያሣየን ነውና እርዱኝ እርዳችኋለው ነው ያለው።ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሞት ለወያኔ መንግስት!

# ዲሞክራሲ የሚከበርበት ሃገር ለመመስረት እንነሳ

**Ribka Lema /Homberg / efze**

ህዝባዊ አመጽን እውን ለማድረግ ሃገር ወዳድ ሃያላት እየጣሩ ያሉት የመለስን አገዛዝ በጥገና ለውጦ አርቆና አለሳልሶ ለማስቀጠል ሳይሆን ከስር መሰረቱ መንግሎ ለመጣል ነው፡፡

ለዚህም ነው ህዝባችን ለአመጽ ሲነሳ የመጀመሪያና የመጨረሻ ግብ ወይንም ጥያቄዎችን አንግቦ መሆን ያለበት፡፡ በመጀመሪያ መፈክሮች ደረጃ “የኑሮ ውድነት ይብቃ“ ዋጋ ይቀነስ ደሞዝም ይጨመር የሃገራችን መሬት ለባእዳን መስጠቱና አርሶአደሩንና ሃገሩን መጉዳቱ ያክትም የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ አፋኝ ድንጋጌዎች ይሰረዙ የህዝብ መሰረታዊ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ይከበሩ በህዝብ ላይ እየተካሄዱ ያሉ ፍጅቶችና አፈናዎች ይቁሙ “የሰርቶአደሩ ጥያቄዎች ምላሽ ያግኙ“ „ሙስና ያክትም“ በሙስና የተሰማሩ ባለስልጣኖች ለፍርድ ይቅረቡ የህዝብ ማህበራት መብታቸው ይከበር በነጻው ፕሬስ ላይ የተደረጉ አፋኝ ህጐች ይሰረዙ ወዘተ ወዘተ የሚሉት መሰረታዊና መነሳትም ያለባቸው አሳሳቢ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ የሃገራችን መሰረታዊ ችግር ምንጩ ግን ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ነው፡፡ አገዛዙ እስከ አለ ድረስ የሃገርና የህዝብ መከራ ሊቀንስ አይችልም፡፡ ስለዚህ በኢትዮጵያ መብትና እኩልነት ዲሞክራሲን ለማስከበር ሌሎች በህዝቡ ላይ የተጋረጡ ችግሮችን ሁሉ ለማስወገድ በቅድሚያ የወያኔን የዘረኛውን መንግስት አገዛዝ በትግል ማሸነፍና መጣል አለብን፡፡

# ማስገደድ ወይም ማስወገድ

**Yohanes Samson /Bad-Hersfeld**

ዛሬ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ በወያኔ ኢሕአዴግ እየደረሰ ያለው አፈናና ረገጣ አስከፊ ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ አምባገነኑ የወያኔ ስርአት ህዝቡን ነጻነት በማሳጣት ዲሞክራሲያዊ መብትን በመግፈፍ ጭቆናው ከመቼውም ጊዜ በበለጠ አጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ በአሁኑ ወቅት በአገራችን ውስጥ ያለው የኑሮ ሁኔታ እና የፖለቲካዊ ቀውስ መፍትሄ እያጣ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ አስከፊ ደረጃ ላይ ነው ያለው የሰዎች መብት የማይከበርበት የብሄረሰቦች መብት የማይከበርበት የሃይማኖት መብት የማይከበርበት የመማር ፣ የመስራት፣ የመጻፍ፣ የመናገር፣ የመምረጥ መብት የሌለበት ሃገር ሆናለች፡፡ ለምሳሌ ብንመለከት በየግዜው የሚካሄድ አገር አቀፍና የክልል ምርጫዎች በአምባገነኑ ወያኔ ኢሕአዴግ መንግስት ይጭበረበራል፡፡ ተወዳዳሪዎች፣ ታዛቢዎችና መራጮች የተለያየ ተጽዕኖዎች ይደርስባቸዋል፡፡ ለምሳሌ በምርጫ 97 ቱ ብሄራዊ ምርጫ የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ምርጫውን ማሸነፍ ተከትሎ ወያኔ ስልጣኑን ላለመልቀቅ ሲል የተለያየ አስቃቂ እርምጃዎችን ወስዷል። ድምጻችን ይከበር ብሎ በወጣው ሰላማዊ ሠልፈኛ ላይ የተኩስ እሩምታ ከፍቶ የብዙሃኑን ህይወት ቀጥፏል፡፡ በሃገሪቱ የተለያዩ ክልሎች የማጐሪያ እስር ቤቶችን በማዘጋጀት እጅግ በርካታ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮችንና አባላትን እንዲሁም ደጋፊዎችን አንገላቷል፡፡ ብዙዎችንም ያለአግባብ ለእስር ዳርጓቸዋል፡፡ ብዙዎችንም ገድሏል። እርምጃቸውና ስርአቱ ምን ያህል አምባገነን ለ21 አመታት አስከፊና ዘግናኝ ጭቆና ደርሶብናል፡፡ አሁንም ከዚህ በተሻለ ሁኔታ ተጠናክረን ካልታገልነው ሃገሪቱን ምስቅልቅሏን ነው ያወጧት ሁላችንም አንዷን ኢትዮጵያችንን ዘር ሃይማኖት ብሄር ሳንል የጋራ ጠላታችንን ልናስወግድ ይገባል፡፡ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር፡፡

# ኦሮሚያ ነጻ እስከምትወጣ ትግላችን አይቆምም

**Habtamu Tesfaye /Fulda**

ወያኔ የጥቂት ባለሃብቶችን እና የታማኝ ካድሬዎችን ጥቅም ብቻ ለማስከበር ብሎም የራሳቸውን ኪስ ለማድለብ የዋሁን እና ምስኪን የኦሮሞ ገበሬ ያለምንም ተተኪ ቦታ እና ያለምንም የካሳ ክፍያ ከለምለም መሬቱ ላይ እየተፈናቀለ ለረሃብ ለስደት ኦሮሞ በታሪኩ ሙሉ የማያውቀውን ለልመናና ለተለያዩ ችግሮች እየዳረጉት ይገኛል፡፡

የመብት ጥያቄ የሚያስነሱ የኦሮሞ ተወላጆች ከግድያ ጀምሮ ለተለያዩ እንግልቶች ይዳረጋሉ በየእስር ቤቱ የሚደርስባቸውን ግፍማ ምን እላችኋለሁ፡፡ እሱን ቤት ይቁጠረው፡፡

ያለምንም ወገናዊ እና ሰብአዊነት ስሜት ህዝባችንን እየበደለ ታሪካችንን ባህላችንን ባህላዊ እሴታችንንና ሃይማኖታችንን ጭምር እያበላሸ የተፈጥሮ ሃብቶቻችንን ለግል ጥቅም እያዋለ ያለውን ሰይጣናዊ እና ክልላዊ መንግስት ማስወገድ የሚቻለው እንደነ ቱኒዚያ፣ ሊቢያ፣ ግብጽ እና የመሳሰሉ ህዘቦች የወሰዱትን ቆራጥ እርምጃ በመውሰድ ብቻ ይሆናል፡፡

እናም ወያኔ እስከ አፍንጫው የታጠቀውን ትጥቅ በማስፈታት ህዝባችንን በሚደርስበት ምሬት ከፍርሃት ቆፈን እንደተላቀቀ እርግጠኛ ነኝ፡፡ከፍርሃት ቆፈን የተላቀቀ ህዝብ ደግሞ መሳሪያ ሳይገታው እራሱን ለማደራጀት እና መሪዎቹን ለመምረጥ ጊዜ አይወስድበትም፡፡

እናም የኦሮሞ ህዝብ ሆይ ወገናችን ህዝባችን ከታሠረበት የመከራ ሰንሠለት በጣጥሰን ለመውጣት ያለን አንድና አንድ አማራጭ ቀዬአችን ድረስ ገብቶ የወረረንን ጠላት ወያኔን ከሠፊው የኦሮሞ ነጻነት ግንባር /ኦነግ/ ጐን በመቆም በትጥቅ ትግል ገርስሶ በመጣል ብቻ ነው እና ዛሬም በጀመርነው ትግል እንበረታለን፡፡በኦሮሞ ሕዝብ እና መሬት ላይ ጥገኛ ሆኖ የኖረውን ዘራፊ መንግስት አንበርክከን ህዝባችንን እና መሬታችንን ነጻ እንወጣለን፡፡ድል ለሠፊው የኦሮሞ ህዝብ !


የአዲሱ ጠ/ሚ
የወደፊት
ህልም....

# አሁንም የጋራ ትግል ያስፈልገናል

**Hana Tadesse Gebremeskel /Münnerstadt**

ብዙሃኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለ21 ዓመታት ጥቂት ወያኔዎች ፈጥረው በሚጥሩት የጭቆና ስርአት ስር ወድቆ በአገሩ ባይተዋር በመሆኑ የመብቱና የራሱ አንደበት ባለቤት ሣይሆን ኑሯል፡፡

በዚህ ምክኒያትም የሚሠማውን መናገር የሚፈልገውን እንዳይመርጥ በሃይል ልጓም ታፍኖ በፍርሃት በጭንቀት እየኖረ ለጥቂት ወያኔዎች አኗኗር ሆኖ ነጻነት እንደናፈቀው በወያኔዎች ተፈርዶበት የመጨረሻው ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡

ይህን ምሬቱን ለመግለጽ ቢፈልግም እንኳ መብትና እድል የለውም ለመብቱና ለነጻነቱ ለእኩልነት መከበር ደፍሮ የወጣውም በአሸባሪነት ወንጀል ተከሶ እስራት ግርፋትና ሞት ይፈርድበታል፡፡

በመሆኑም ይህንን በደልና ግፍ በግልጽ ለመቃወም ለማውገዝ በኢትዮጵያ ውስጥ ሆኖ አልተቻለም ያለው እድል ከሞት ያመለጠው ነጻነትና ዲሞክራሲ ፈላጊ መሠደድና በውጭ አገር ሆኖ ብሶቱን ለውጩ አለም ሕዝብና መንግስታት በመግለጽ የአለብንን ወገናዊ አደራና ግዳጁ መወጣት ነው፡፡ ስለዚህ በህብረት ሆነን ማንኛውም ኢትዮጵያዊ እጅ ለእጅ ተያይዘን ትግላችን አብረንህ ከአንተ ጐን እንዳለን እየተሠማህ በተጠናከሪ ትግል ቀጥል መለስ ቢሞት ሃይለማርያም ደሣለኝ ቢተካ ጉልቻ ቢቀያየር ወጥ አያጣፍጥምና የዘረኛውን ወያኔ አሻንጉሊት ድርጅት ከስር ለመገርሠስና ለመጣል ተቃውሞህንና ትግልህን በበለጠ አጠናክር ድር ቢያብር አንበሣ ያስር ነውና በርታ ከጐንህ ነን፡፡

# የወያኔ የጥፋት አገዛዝ

**Mulugeta Gashaw / Heppenheim**

የብሄር እና ብሄረሰቦችን መብት አስከብሬያለሁ የሚለው የወያኔ መንግስት አንድን ብሄር ከሌላው ብሄር ጋር በጠላትነት እንዲተያይ ማድረጉ ሳያንስ ይባስ ብሎ ወደ ሃይማኖት በመግባት በቤተክርስቲያን በገደማቶች በሙስሊሙ የእምነት ስርዓት ውስጥ በመግባት መበጥበጡን ቀጥሏል ህዝቡም ተቃውሞውን እንዳያሰማ በየሰፈሩ በፌደራል ፖሊስ ተከቦ አፈሙዝ ተደግኖበት የመረረው ህዝብ ይሄን ከማይ ብሎ እግሩ ወደ አመራው ስደትን መርጧል፡፡ ሃይ ባይ ያጣው የወያኔ መንግስት ባለስልጣናት ህዝቡን ግራ በማጋባት መምራታቸውን ቀጥለዋል፡፡ ህዝቡም የወያኔ የህዋሳት ፕሮፓጋንዳ እና የውሸት ተስፋ ተሰላችቶ ትክክለኛ ለሃገር የሚበጅ መሪ በመናፈቅ ዝምታን መርጦ እየኖረ ነው፡፡

ወያኔ የስልጣን ዘመኑን ለማራዘም በተለያየ ጊዜ የተለያየ አጀንዳ በመፍጠር ህዝባችንን እንዲሁም የለውጥ ሃይል የሆነው ወጣት በአንድ ሃሳብ ወደ ልማት ተሰማርቶ ሃገሪቱን ለዘመናት ያልተላቀቃትን ድህነት እንዳያሸንፍ የዕድሜ ማራዘሚያ መሳሪያ አድርጐታል፡፡

መንግስት መስሪያ ቤት ለመቀጠር፣ ስልጣን ለመያዝ እድገት ለማግኘት የግል ጉዳዩንም በትክክል ለማስፈጸም የወያኔ መንግስት አባል መሆን ግድ ይላል፡፡ ያለበለዚያ የፈለገውን ያህል ትጉህ ሰራተኛ ቢሆንም ሁሉንም በደል ችሎ በቅንነት ለወገኑ ያቅሙን ያህል ማበረከቱን ቢፈልግም በሚሰራው ስራ እንቅፋት በመሆን በጠላትነት አይን በማየት በሃገሩ ላይ እንደ ሁለተኛ ዜጋ ተቆጥሮ ይኖራል፡፡ ነገር ግን የወያኔ ካድሬ የሆነና የነሱን ዲስኩር የሚያስተጋባ ሂሊናውን ሸጦ የሃገር እና የህዝብን ጥቅም ችላ በማለት ለግል ጥቅሙ ብቻ በማሰብ የሚኖረው በዝቷል፡፡ስለዚህ ከነገ ተጠያቂነት ለማምለጥ ዛሬ የበኩላችንን ለመወጣት እንዘጋጅ።

# ቤል ተዋረደ፥ ናባው ተሰባበረ

## /Bel boweth down, Nebo stoopeth/

**Dawit Fanta /Engineer/ Germany**




በአንድ ወቅት ገጣሚና ደራሲ በዕውቀቱ ስዩም "ይህ አዲስ አበባ አይደለም፥ይህ የገጠር ቀበሌ ነው" የተሰኘ መጣጥፍ ፅፎ ነበር።እናም በዚያች "ሥርዓት አልበኝነት" በነገሰባት የገጠር ቀበሌ ውስጥ የሂሳብ መምህሩ ከመቅፅበት ተነስተው የስዕል መምህር ሲሆኑ ይታያል።በርግጥም የህግ የበላይነት ባልሰፈነባት በዚያች የገጠር መንደር የሂሳብ መምህሩ የስዕል መምህር መሆን ሳያንሳቸው ተማሪዎቻቸውን ሲያሰቃዩ ይስተዋላል።እንግዲህ እስኪ ይህን ትንሽ ከድርሰትነቱ ወጣ ብናደርገውና የገጠር ቀበሌዋን የሂሳብ መምህር ወደ አዲስ አበባ ብናመጣቸው እንዲሁም እሳቸውም በለመዱት "ህገ-አራዊት" ልመራ ቢሉ በአንፃራዊ ዕድገትና ሥልጣኔ ላይ ያለው የአዲስ አበባ ሰው እንዲህ የሚላቸው ይመስለኛል፡-"ይህ የገጠር ቀበሌ አይደለም፥ይህ አዲስ አበባ ነው!"

በተመሳሳይ ወደ መንበረ መንግስት ከመጣ ከሁለት አሥርት አመታት በላይ ያስቆጠረው የወያኔ መንግስት በኢትዮጵያ የዜጎችን ሰብዓዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በመጣስ ብዙዎችን ለእስር፣ለእንግልትና ለስደት ከማብቃቱም በላይ በግፍ የገደላቸው ዜጎች ቁጥር ቀላል የሚባል አይደለም።በመሆኑም የወያኔ አገዛዝ ሀገራችን ኢትዮጵያን የፍትህ አልባና የአፈና ተምሳሌት አድርጓት ይገኛል።

ይሁን እንጂ ይህ ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብትን በኃይል የመጨፍለቅ ወያኔአዊ አባዜ ባህር ተሻግሮ በምድረ አሜሪካ በቅጥር ነፍሰ ገዳዮቹ አማካኝነት በጋዜጠኛና አክቲቪስት አበበ ገላው ላይ ሊፈፀም የነበረውን የግድያ ሙከራ የአሜሪካ የፌደራሉ የምርመራ ቢሮ እንዳከሸፈው ኢሳት በጃንዋሪ 08, 2013 የዘገበው።እዚህ ጋር ነው እንግዲህ ለወያኔ **"ይህ አዲስ አበባ አይደለም፥ይህ አሜሪካ ነው!"** ማለት።

የህግ የበላይነት በሰፈነባት ሀገር በሀይልና በህገ-አራዊት በመነዳት ንፁሃን ዜጎችን ለመግደል መሞከር አለማቀፋዊ አሸባሪነት ነው!!!በህግ ሽፋን አንቀፅ 652/2009ን እየጠቀሰ ንፁሃን ጋዜጠኞችን በአሸባሪነት በመወንጀል ወደ እስር ቤት ሲወረውር የነበረው ወያኔ ዛሬ ቅጥር ነፍሰ-ገዳዮችን በመመልመል በአንዲት ሉዓላዊት ሀገር ውስጥ የሽብር ተግባር ሊፈፅም ሲያሴር መገኘቱ መለስ ዜናዊ በሮናልድ ሬገን ህንፃ ከተዋረደበት የሜይ አስራስምንቱ ስብሰባ ቀጥሎ ወያኔን እርቃኑን ያጋለጠ ሌላ አጋጣሚ ሲሆን ለወያኔ ተጨማሪ የፖለቲካ ኪሳራ፥ለአባላቱም ሌላ ስብራት ሆኗል።**ቤል ተዋረደ፥ናባው ተሰባበረ እንዲል ነብይ በመፅሐፉ።**

በዚህ አጋጣሚ የወያኔን የሽብር ተግባር በእንጭጩ በመቅጨት የአበበ ገላውን ህይወት ለታደጓት የአሜሪካኑ የፌደራል የምርመራ ቢሮ ሠራተኞች ያለንን አክብሮት እየገለፅን **"የወይናችንን ቦታ የሚያጠፉትን ቀበሮዎች፥ጥቃቅኑን ቀበሮዎች አጥምዳችሁ ያዙልን"** መልዕክታችን ነው!!!ቸር እንሰንብት።

# የኢህአዴግ ካድሬዎችና ፖሊስ ህዝቡ የምርጫ ካርድ እንዲወስድ እያስገደዱ ነው

**Dawit Demelash/Norway**

በመጪው ሚያዝያ 2005 ዓ.ም. ለሚደረገው የአዲስ አበባ መስተዳደርና የአካባቢ ምርጫ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች

በግድ ምርጫ ካርድ እንዲወስዱ እየተደረጉ መሆኑን መረጃዎች ጠቆሙ፡፡

የደረሱ መረጃዎች ለማረጋገጥ በተለያዩ የአዲስ አበባ አካባቢዎች የተዘዋወሩት የጋዜጣው ዘጋቢዎች እንዳረጋገጡት የኢህአዴግ የወረዳ ካድሬዎችና ፖሊስ ከፍተኛ ግዳጅ እንደተሰጣቸውና በየመንደሩ እየዞሩ ቅስቀሳና ማስፈራሪያ እየሰጡ መሆናቸውን ከተለያዩ ምንጮች አረጋግጠዋል፡፡ ነዋሪው በበኩሉ ተወዳዳሪ በሌለበትና ውጤቱ በታወቀ ምርጫ ካርድ ውሰዱ ብሎ መንግስት ማስገደዱ እንዳሳዘናቸው እየገለፁ ይገኛል፡፡

በተለይ በአዲስ አበባ በሚገኙ የተለያዩ ክፍለ ከተሞች የኢህአዴግ የወረዳ ካድሬዎችና ፖሊስ በየመኖሪያ ቤቱና በየንግድ ተቋማት በመዞር የምርጫ ካርድ የወሰዳችሁና ያልወሰዳችሁ ተመዝገቡ እያሉ እያስገደዱ መሆኑን ነዋሪዎች ገልፀዋል፡፡
የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የህዝብ ግንኙነት ኢህአዴግን ወክለው ምርጫ የተወዳደሩ ከመሆናቸውም በላይ ነባር የብአዴን/ኢህአዴግ ታጋይ መሆናቸው አይዘነጋም፡፡

ታዲያ በምን መልኩ ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ይካሄዳል ብሎ መጠበቅ ከእባብ እንቁላል እርግብ መጠበቅ ነው በማለት 33 ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከምርጫው በኋላ ሊደርስ የሚችለው አደጋ ፈርተዋል፡፡

ዋነኞቹ 33 ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከምርጫው ሂደት በፊት ምርጫ ቦርድ ጥያቄያችንን ሊመልስልንና የኢህአዴግ ጉዳይ አስፈፃሚነቱን ትቶ ሁሉንም ፓርቲዎች በእኩል አይን ማየት ካልቻለ ወደ ምርጫ አንገባም የሚል የጋራ አቋም እንደያዙ ይገኛሉ፡፡

# የለውጥ ጊዜ ተቃርቧል

**Abel Tesfa (HOF)**

አምባገነኑ የኢህአዴግ መንግስት እያደረገ ያለውን ግፍና ጭቆና አሁንም ቀጥሏል።መንግስት የህዝብን ነጻነት፣መብትና ህልውና እጅግ አደገኛ ሁኔታ ላይ ነው ያለው።በጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ዜናዊ የሚመራው የኢህአዴግ መንግስት የሳቸውን የህልፈት ህይወት ተከትሎ እሳቸውን ተከተው ስልጣን ላይ የወጡት አሻንጉሊት የተባሉትን ከማድረግ አልተቆጠቡም።በቅርብ ጊዜ ውስጥ የሚታየው የኢህአዴግ ውዥንብር በሃይማኖት ጣልቃ በመግባት እኛ በመረጥንላችሁ የሃይማኖት አባት ተመሩ እያለ የሙስሊሙን ህዝብ መብት በመርገጥ መብቱን ለመጠየቅ የወጣውን በማሠርና በመግደል ላይ ናቸው።መንግስት ጭቆናውን በፍጥነት ማቆም አለበት።

# ስደት እስከ መቼ?

**Almaz Sebehat Lema (Kronach)**

ውድ አንባቢያን እንደምን ከርማችኋል? አምባገነኑ የወያኔ መንግስት በአሁኑ ወቅት በሰፊው ህዝብ ላይ እየፈፀመ ያለው ኢ-ሰብዓዊና ኢ-ዲሞክራሲያዊ ተግባር እየሰፋ መጥቷል።የወያኔ መንግስት በሃገሪቱ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችን ጠንካራ ሆነው እንዳይታገሉት ፓርቲዎችን በመበታተንና በማፈራረስ እንዲሁም አመራሮችን በማሠር፣በማዋከብና በማስፈራራት ፍፁም ደህንነት እንዳይሰማቸው በማድረግ ጠንካራ የተቃዋሚ ፓርቲ እንዳይኖር በማድረግ ላይ ነው።ከዚህም በተጨማሪ የዜጎች መሰረታዊ ሙብቶች የመናገር፣የመፃፍ፣የመሰብሰብና ሃሳብን በነፃ የመግለፅ መብት ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ ተነፍገው ይገኛሉ።በህዝቡ ላይ የሚደርሰውን ግፍና ጭቆና በጽኑ የሚቃወሙትንና የሚታገሉትን ውድ ኢትዮጵያውያንን እና በሃገሪቷ ውስጥ ያለውን እውነታ ለዓለም የሚዘግቡ ጋዜጠኞችን ወደ ወህኒ አውርዷል።ከአምባገነኑ የግፍ አገዛዝ ለማምለጥና ህይወታቸውንም ለማትረፍ ሲሉ ዕድል ቀንቷቸው ከሃገር የወጡትም የሚወዱትን ህዝብና ሃገራቸውን ትተው ህይወታቸውን በስደት ይገፋሉ።ታዲያ ወገኖቼ በትውልድ ሃገራችን በነፃነት ከምንወደው ህዝባችን ጋር መኖር ካልቻልን ስደት እስከመቼ?
ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!

# ከአምባገነንነት ወደ አምባገነንነት

**Berhanu Baue/Schweinfurt**

እንደ መነሻ በ1983ዓ.ም በወርሃ ግንቦት መንግስትን በሃይል የተቆጣጠረው ኢህአዴግ ከጥቂት ወራት በሁዋላ 22ኛ ዓመቱን ይደፍናል።በእነዚህ ዓመታት አገዛዝ ላይ የነበረው ሃይ በሁለት ይከፈላል።ቡድናዊና ግለሰባዊ።
በእነዚህ ዓመታት ኢህአዴግ ለኢትዮጵያ ህዝብ ምንም የጠቀመው ነገር የለም።በዚህም ፋንታ በህወሓት አመራር አባል የተያዘው ቡድናዊ አክራሪ ብሄረተኛ ከመሆኑም በተጨማሪ ለህዝብ ከመቆም ይልቅ ለቡድን የቆመ ፓርቲ መሆኑን ያሳየናል።
አሁን ደግሞ በአቶ መለስ ሞት የተተካው ጠቅላይ ሚኒስትር ከአስመሳይነት ወጥቶ ምክንያታዊ ወዳልሆነ ጉልበተኛነት ማዘንበሉን ከሚያመለክቱ ነጥቦች ውስጥ የመጀመሪያው የሙስሊሞች የሃይማኖት ነፃነት ይከበር ጥያቄን በሃይል በማፈን ተፅዕኖ እየፈጠረ ይገኛል።
ሌላው ከመለስ ዘመን አስመሳይና አምባገነን አገዛዝ የተለየ መሆኑን የሚያመለክተው በአገሪቱ የፕሬስ ታሪክ የመጀመሪያ በሆነ መልኩ የፕሬስ ነፃነትን በማፈን እራሱ ያፀደቀውን አንቀፅ በመጣስ በቅርቡ የፍትህ ጋዜጣን የወረሱበት መንገድ ይገኛል።እነዚህ ሁሉ በአደባባይ የተፈፀሙ ህገወጥ ድርጊቶች አዲሱ አስተዳደር እንደ መለስ ዘመን ለይስሙላ እንኳ ለህጋዊነት ያለመጨነቁን ያሳያል።በአጠቃላይ ማሳያዎቹ በመለስ መንግስትና በወራሾቻቸው መካከል ያለውን ተመሳሳይነት የውጤት አንድነት እንጂ የአካሄድ ያለመሆኑን ያመለክታል።
ስለዚህ እነዚህን ከዘመን የተጣሉ ጠባብ ብሄረተኞች ከአምባገነንነት ወደ አምባገነንነት እንዳይቀጥሉ ተባብረን እድሜያቸውን ማሳጠር አለብን። ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር።

# መሪ የሌለው መንጋ ይበተናል።

**Addisalem Tegne Abera (Kronach)**

መሪ ማለት ህዝቡን መንጋውን የሚጠብቅ እንዳይራቡ እንዳይጠሙ የሚጠብቅ ማለት ነው።አሁን ግን የተገላቢጦሽ ሆኗል።የምናየው፣የምንሰማው መሪ ወይም የሀገር ገዢ ህዝቡን አንቀጥቅጦ፣ረግጦ፣ጨቁኖ የሚያኖር ወይም የሚገዛ መሪ በማለት ይጠራል።ታዲያ ህዝቡም ሰብዓዊ ረገጣ እና አፈናና ጭቆና ሲበዛበት ይሰደዳል ይኮበልላል።በተለያዩ የአለማችን ክፍሎች የኢትዮጵያ ልጅ የሌለበት የለም ብንል ማጋነን አይሆንም።ለምን ቢባል በተለያየ ችግር ምክንያት ሀገራቸውን ለቀው ይሰደዳሉ።ለዛሬ አንዷት ኢትዮጵያዊት እህታችን በሣዑዲ አረቢያ ውስጥ አንገቷ በሰይፍ ተቀልቶ ሞታለች።ታዲያ መሪ ተቆርቋሪ ቢኖራት ትሠዋለች?ከሀገሯ ያልፍልኛል ቤተሰቤን ወንድም እህት እረዳለሁ ብላ ከሀገሯ ተሰደደች።እርሷ ግን በሚያሳዝን ሁኔታ በሰይፍ አንገቷን ታረደች።ውድ የኢትዮጵያ ልጆች አንድ መሪ አንድ የሀገር አስተዳዳሪ የዜጋውን መብት ቢያንስ ለምን ብሎ እንኳ አይጠይቅም።ታዲያ መሪ አለን ለማለት ያስደፍራል?አያስደፍርም።ህዝባችንን ወገናችንን እግዚአብሔር ይጠብቅ።አበቃሁ።

# በኢህአዴግ ስርዓት የለም ተጠያቂነት!

**Samuel Menase/Münnerstadt**

በፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ስርዓት ውስጥ የሚተዳደሩ አገራት ዋነኛ መገለጫቸው የግልፀኝነትና ተጠያቂነት እጦት ነው።ግልፀኝነትና ተጠያቂነት በሌለበት በፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ስርዓት ውስጥ

የሚተዳደሩ አገራት ዋነኛ መገለጫቸው ደግሞ ሙስና ነው።በእነኚህ አገራት ሙስና የማህበራዊ ግንኙነትና የመንግስታዊ አገልግሎቶች ማስፈጸሚያ መሳሪያ ነው።

በእርግጥ አንዳንድ ፈላጭ ቆራጭ አገሮች ሙስናን የፖለቲካ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ ስልት አድርገው ይጠቀሙበታል።የዚህ ትልቁ ማሳያ ምሳሌያችን ደግሞ የኢህአዴግ መንግስት ነው።ከግልፀኝነትና ተጠያቂነት እጦት ጋር በተያያዘ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ የሙስና መጠኑ በምን ያክል ደረጃ ላይ እንደደረሰ መገመት እንደሚከብድ ጥናቶች ይገልፃሉ።ስለዚህ በአገራችን ሙስና ያለበትን ደረጃ ለማወቅና ችግሩንም ለማጥፋት ግልፀኝነትና ተጠያቂነት መስፈን አለበት።ከሙስና ለፀዳች አገር ግንባታ የበኩላችንን አስተዋፅኦ እንድናደርግም መልዕክቴ ነው።

# ታሪክን እንጠብቅ

**Metasebia Keflu /Kronach**

ሀገራችን ኢትዮጵያን ዳር ድንበሯን፣ታሪኳን፣አንድነቷን እና ባህሏን ወገኖቿ ጠብቀው ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲወርድ ሲዋረድ የቆየ ቢሆንም ታሪኳን እና ባህሏን ለማጥፋት የወያኔ መንግስት በአሁኑ ወቅት እጅግ እየተንቀሳቀሰ ነው ያለው።እርሱም ክርስቲያኑ በቤተክርስቲያን ሙስሊሙ በመስጊድ ተዋዶ እና ተፋቅሮ ፈጣሪውን ለማመስገን አልቻለም።ለምን ቢባል ዙሪያውን በመሣሪያ እየተጠበቀ ሁልጊዜ በስጋት ነው የሚኖረው።የሚገርመው ውድ የኢትዮጵያ ልጆች እና ታሪክ የሠሩ ጀግኖቿ ሀውልት በስማቸው ተሰርቶ እና ተሰይሞ የነበረውን ሃውልት እያፈረሱ እና እየናዱ ይገኛሉ።ይህ የሚያሳየው ታሪክ የሰሩትን አባቶቻችንን ታሪካቸውን ለማጥፋት ቆርጠው ተነስተዋል።ነገር ግን እኛ ደግሞ ታሪክ አክባሪ እና ታሪክ ሠሪ መሆን አለብን።ይህንንም ለማድረግ እኔ አንተ አንቺ መባባሉን ትተን በጋራ ትግል ከታሪክ ተወቃሽነት ለማዳን ሀገራችንን በጋራ ታግለን በጋራ ስንጠብቃት ብቻ ነው። ይህ ከሆነ ሀገራችንን ለትውልድ ማስተላለፍ እንችላለን።አለበለዚያ ግን ይህን ዘረኛ እና ታሪክ አጥፊ መንግስት ያለምንም ርህራሄ ልናስወግደው እና በቃ ልንለው ይገባል።ዝም ብለን ካየን እኛም የታሪክ አጥፊው መንግስት ተመልካቾች እንዳንሆን ጠንክረን በጋራ አብረን እንታገል።እንዋጋ የጋራ ክንድ የጋራ ትግል ውጤቱ ያማረ ነውና እንበርታ እንጠንክር።አበቃሁ።

# የኢትዮጵያ ህዝብና በሃገሩ የመኖር መብት

**Eden Dawit Kidane/Gießen**

በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ህዝብ በአገሩ የመኖርና በአገሩ በፈለገበት ስፍራ ወይ መኖሪያውን መስርቶ የመኖር ዋስትናው እስከመገፈፍ ተዋርዶም ከመኖሪያ ቤት በመባረር ላይ ይገኛል።ይህ ህዝብ መሄጃ መደበቂያ ሲያጣ ሃገሩን ጥሎ ላለመውጣት በትግል ላይ ይገኛል።ነገር ግን በሌላ መልኩ በመንግስት የሚደረግበት ግፍና መዋከብ ምክንያት አቅም ያለው በገንዘቡ አቅም የሌለው በቻለው መንገድ በመሰደድ ላይ ይገኛል።

ባለፉት 20 ዓመታት የኢትዮጵያ ህዝብ እያየ ያለውን ስቃይና መጎሳቀል በየትኛውም ዓለም ታይቶ አይታወቅም።ህዝባችን ድምፁን ለማሰማት በተለያዩ መንገዶች ይመክራል።በየስቴዲየሙ በየውድድር ቦታዎች ሁሉ ተቃውሞውን እያሰማ ይገኛል።

እኛስ ህዝባችንን ለማገዝ ምን እያደረግን ነው? የኢትዮጵያ ልጆች ድምፃችንን ለዓለም የኢህአዴግን ግፍ ማጋለጥ አለብን።ህዝባችን አደራውን ለእኛ ሠጥቷል።ከኛ የሚጠበቀውን መፈፀም ግዴታችን ነውና።አንድ ሆነን ይሄንን ጨፍጫፊ መንግስት በቃህ እንበለው።በትግላችን ሁሉ እገዛውን የሚሰጠን ኢህአፓ ከጎናችን ይቆማል።ትግላችን ይቀጥላል።ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

# መለስ ከመቃብር ሆኖ ኢትዮጵያን እያስተዳደረ ነው

**Fissha Tsion Hailegeberile/ Kronach**

እንደሚታወቀው ላለፉት ሀያ አመታት የወያኔ መንግስት ወይም የአቶ መለስ ዜናዊ አስተዳደር ሀገራችንን ሲያስተዳድር ቆይቷል።ነገር ግን በስልጣን ዘመኑ ብዙም አመርቂ ዕድገቶች አልተመዘገቡም።ሀገራችንም እምብዛም የተለወጠ ነገር የለም ነገር ግን የማይካደው የኢትዮጵያን ውድ ልጆች ብሔር ብሔረሰቦች በዘር ከፋፍሏል።ትልቁ ለውጥ ለስልጣን ማራዘሚያው የሚሆነውን ሥራ ሠርቷል እንጂ የሀገራችን ዕድገት አልታየም።ታዲያ አቶ መለስ ዜናዊ በህይወት እያሉ ሀገራቸውን ያስተዳድሩ የነበረው ብዙ በማውራት እንጂ ብዙ በመስራት አልነበረም።ለምን?ዓለም የሚያውቃቸው በተናጋሪነታቸው ሲናገሩ አንደበተ ርቱዕ ቃልን በቃል የሚያጣቅሱ ጎበዝ መሪ መሆናቸውን አለም ያውቃቸዋል።አዎ ሙት ወቃሽ አያድርገን እንጂ እኛም ስለተናጋሪነታቸው እንመሰክራለን።ለዚህ ነው ሙት ወቃሽ አያድረገን ያልኩት።ታሪክ ወቃሽ ግን ያድርገን። ለምን ቢባል እስኪ ምን?አቶ መለስ ሞተዋል ቢያንስ በሀገራችን ትንሽ የስርዓት ለውጥ አይደረግም ባይበዛ እንኳን በጥቂቱ በሀገሪቱ ሲባል ታዲያ ይህ የሚያሳየው አሁንም አቶ መለስ ዜናዊ ከመቃብር በታች ሆነው ኢትዮጵያን እያስተዳደሩ ነው ብንል ምንም ስህተት የለውም።አበቃሁ። አመሰግናለሁ።

# የፕሬስ አፈናው ይቁም

**Abebe Demelash /Hof**

ምንም እንኳን የወያኔ መንግስት በራሱ ህገ-መንግስት ላይ ዜጎች ሃሳባቸውን በነፃነት የመግለፅ መብትን ቢፈቅድም በተግባር የሚታየው ግን ከዚህ በተቃራኒ ነው። ይባስ ብሎም በአሁኑ ወቅት ሀገራችን ኢትዮጵያ ጋዜጠኞችን በማሰርና ከሀገር እንዲባረሩ ከሚያደርጉ ጥቂት ሀገራት የቀዳሚነቱን ስፍራ እንድትይዝ ሲያደርጋት የወያኔ መንግስትም የሀሳብ ልዩነትን በፀጋ የማያስተናግድ ይልቁንም በሃሳብ የሚቃወሙትን በሙሉ በአሸባሪነት የሚፈርጅ፣ጋዜጠኞችን በሃሰት ክስ ወደ ወህኒ የሚያወርድ ሆኗል።የወያኔ መንግስት በዚህ ሳይወሰን በቅርቡ ሁለት የነፃ ፕሬስ ጋዜጦችንና አንድ መጽሔትን ማለትም ፍትህ ጋዜጣ፣ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ እንዲሁም አዲስ ታይምስ መፅሔት እንዳይታተሙ ከልክሏል።

በአሁኑ ወቅት ዜጎች ሃሳባቸውን በነፃነት እንዳይገልፁ ከመታፈናቸውም በላይ መረጃ እንዳያገኙም ተከልክለዋል።

በመሆኑም ይህ በነፃው ፕሬስ ላይ የሚደረገው አፈና እንዲቆም፣ዜጎችም በነፃነት ሃሳባቸውን እንዲገልፁ፣መረጃም በነፃነት የማግኘት መብታቸው እንዲረጋገጥ የወያኔን መንግስት በጋራ ልናስወግደው ይገባል።

# ወያኔና የፍትህ ሥርዓቱ

**Liya Yosef (Klümba)**

በአንድ አገር የፍትህ ስርዓት ውስጥ ህግ አውጪ፣ህግ ተርጓሚና ህግ አስፈፃሚ አካላት ሲኖሩ ከነዚህ ሶስት አካላት የአንዱ ኃላፊነቱን በአግባቡ አለመወጣት በአጠቃላይ የፍትህ ሥርዓቱ ላይ ጉልህ ተፅዕኖ ያሳድራል።

ለምሳሌ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ እየታየ ያለው የህግ ተርጓሚ ማለትም ፍርድ ቤቶችና የህግ አስፈፃሚው (የፀጥታ ኃይሎች) በፖለቲካ ተፅዕኖ ሥር መውደቃቸው በኢትዮጵያ ያለውን የፍትህ ሥርዓት ሚዛናዊነት አሳጥቶታል።

የፀጥታ ኃይሎች ያለ በቂ ማስረጃ በፖለቲካ ወገንተኝነት በመመራት ብቻ ዜጎችን ላልተወሰነ ጊዜ ከማሰራቸውም በላይ ፍርድ ቤቶች ዜጎችን ያለአንዳች የህግ አግባብ የዋስትና መብት በመንፈግ ሰብዓዊ መብታቸው ተገፎ ፍትህን በማጣት እየማቀቁ ይገኛል።

ይህ የተቋማቱ ከፖለቲካ ወገንተኝነት ነፃ ያለመሆን በዜጎች ላይ እየደረሰ ካለው የሰብዓዊ መብት ጥሰት ባሻገር በሀገሪቱ ውስጥ የዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብና ስርዓት እንዳይኖር ማነቆ ሆኗል።

በተለይ ከቅርብ አመታት ወዲህ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትን በሀሰት ክስ ማሰር፤ከዚያም በተፅዕኖ ስር በማድረግ በሚዲያ ያላጠፉትን ጥፋት እንዲያምኑ በማድረግና በማህበረሰቡ ውስጥ ተደማጭነታቸውን በማሳጣት ከእስር መፍታት ሌላው የህግ ስርዓቱ ሚዛናዊነትን ማጣትና ከፍትህ ይልቅ የወያኔ ፍላጎት ማስፈፀሚያ መሳሪያ መሆኑን ያሳያል።

በመሆኑም ፍትህ አልባ፣ዜጎቿ ሰብዓዊ መብታቸው ተረግጦ የሚኖሩባት እና በዴሞክራሲ እጦት እየማቀቀች ያለችውን ሀገራችንን ነፃ የምናወጣበት ጊዜው አሁን ነው። ስለሆነም በተገኘው አማራጭ ሁሉ ይህንን አስከፊ የወያኔ ስርዓት መጣል ይኖርብናል።

# አንቀጽ 27-የወረቀት ላይ ነብር

**Yohannes Selamu Benti (Hof)**

በአንድ ሀገር የፍትህ ሥርዓት ውስጥ የህግ አውጪው አካል የቱንም ያህል ምርጥ የተባለ ህግ በወረቀት ላይ ቢያረቅ እንኳን ህጉ ወደ ተግባር ካልተለወጠ ዋጋ ሊኖረው አይችልም።

ለምሳሌ የወያኔ መንግስት ባፀደቀው ህገ መንግስት ላይ በተለይም በአንቀጽ 27 መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ እንደማይገባ ቢደነግግም በተግባር የሚታየው ግን የወያኔ አስተዳደር በክርስትናም ይሁን በእስልምና ሃይማኖቶች ጉዳይ ጣልቃ በመግባት አመራሮቻችሁን ´´እኔ ካልመረጥሁ'' እያለ ይገኛል።
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በውጪ እና በሀገር ውስጥ የሚገኙት ሲኖዶሶች የሚያደርጉት እርቅ ከግማሽ መንገድ በላይ ከተጓዘ በኋላ ያለውጤት እንዲቋረጥ የተደረገው በወያኔ ጣልቃ ገብነት ነው።ከዚህም ባሻገር የቤተክርስቲያኗ ይዞታ የሆኑ ታሪካዊ ገዳማትን በልማት ስም ማፈራረስ፣መነኮሳቱን ማሰርና ማሰቃየት የስርዓቱ መገለጫ ሆኗል።
በሌላ በኩል ከአንድ አመት በላይ ያስቆጠረው የ``ድምፃችን ይሰማ`` የሙስሊሞች ተቃውሞ እንዲሁ መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ የሚያደርገው ጣልቃ መግባት ውጤት ነው።ስለሆነው የሃይማኖት ነፃነት በኢትዮጵያ ይከበር ዘንድ የወያኔን መንግስት በጋራ ልንታገለው ይገባል።

# የምን ምርጫ?

**Wube Alemayehu/Münnerstadt**

ኢህአዴግ ወደ ስልጣን ከመጣበት ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ በኢትዮጵያ ከሰባት ያላነሱ ሀገራዊና ክልላዊ ምርጫዎች ተካሂደዋል።በተለይ ከ1997 ዓ.ም ምርጫ በሁዋላ በኢትዮጵያ እየተደረገ ያለውን ምርጫ "ምርጫ" ብሎ መጥራት እንደሚከብድ በርካታ ምሁራን ይገልፃሉ።

**ምርጫ ያለተወዳዳሪዎች**

**በሚያዝያ** 2000ዓ.ም በተደረገው የወረዳና የአካባቢ ምርጫ ኢህአዴግ ያለምንም ተቃዋሚ ፓርቲዎች ተሳትፎ ምርጫውን 99% በማሸነፍ በመላ አገሪቱ ከ3.6 ሚሊዮን በላይ የአካባቢ ምክር ቤት ወንበሮችን በበላይነት ተቆጣጥሯል።የአካባቢ ምክር ቤቶች በዜጎች የዕለት በዕለት ኑሮ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ሊፈጥሩ የሚችሉ ናቸው።እነኚህ ምክር ቤቶች ስልጣናቸውን በመጠቀም እንደ ደህንነት የፍርድ ቤቶች አገልግሎትና ሌሎች ወሳኝ የሚባሉ ማህበራዊ አገልግሎቶችን የመወሰን አቅም አላቸው።

**ታሪክ ተደገመ**

በግንቦት 2002ዓ.ም በተደረገው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምርጫ ኢህአዴግና አጋር ድርጅቶቹ ከ547 መቀመጫዎች 545ቱን ሲያሸንፉ ተቃዋሚዎች ግን 1 መቀመጫ ብቻ ነበር አሸነፉ የተባሉት።አንዱ ወንበር ደግሞ በግል ተወዳዳሪ የተያዘ ነው።

**በ2005ዓ.ም ታሪክ ይደገማል**

በዚህ ዓመት በመላ አገሪቱ የአካባቢና የሚሟያ ምርጫ ይካሄዳል።ምርጫው ነፃና ገለልተኛ የማይሆንባቸው አንዳንድ ምክንያቶች:-1) ኢህአዴግ የብሄራዊ ምርጫ ቦርድ አባላት ስብጥርን በሚመለከት ከዋነኛ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር ስምምነት አለመድረሱ 2) በየክልሉና አካባቢው የሚገኙ የምርጫ አስፈፃሚዎች ከገዕው ፓርቲ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያላቸው መሆን 3) የየአካባቢው ባለስልጣናት ህዝቡ ድምፁን ለኢህአዴግ እንዲሰጥ እንደ መኖሪያ ቤት ማዳበሪያ የምግብ እርዳታና ሌሎች ጥቅማጥቅሞች በመደለል ላይ መሆናቸው 4) በምርጫ ቅስቀሳው ወቅት የመንግስት ሰራተኞችንና መገልገያ መሳሪያዎችን እንዲሁም የህዝብ መገናኛ ብዙሃንን በመጠቀም ምርጫውን ሙሉ ለሙሉ ለማሸነፍ ጥረት የሚያደርግ መሆኑ ይጠቀሳሉ።

# አፈና ለነፃነት የሚደረገውን ትግል አያቆመውም!

**Yared Tadese Abraham /Hof**

እንደሚታወቀው ከምርጫ 97 ወዲህ የወያኔ መንግስት በሀገራችንና በዜጎቿ ላይ እያደረገ ያለው አፈና ከጊዜ ወደጊዜ እየከፋ መጥቷል።ጋዜጠኞች ይታሰራሉ፣የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅት አመራሮች ይታሰራሉ፣የነፃ ፕሬስ ጋዜጦች ከህትመት ይታገዳሉ፣የመሰብሰብ እና በነፃነት የመደራጀት መብት ተነፍጓል፣መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ ይገባል፣የመንግስትን በሃይማኖት ጣልቃ መግባት የሚቃወሙትን በአሸባሪነት ይከሳል…….ወዘተ።
ይሁን እንጂ ለህዝቦች ዴሞክራሲያዊ መብት መከበር ትግቢውን ምላሽ ከመስጠት ይልቅ በአምባገነናዊ ማንአለብኝነት ወያኔ እየተከተለ ያለው አካሄድ ለነፃነታችን መሳካት የምናደርገውን ረጅሙን ጉዞ አያደናቅፈውም።በመሆኑም በኢትዮጵያ ውስጥ እውነተኛ የፌደራል ሥርዓት ተዘርግቶ ሁሉም ዜጎች በነፃነትና በእኩልነት የሚኖሩባት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ እውን እስክትሆን የምናደርገው ትግል ይቀጥላል።ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!

# በተባበረ ክንድ የወያኔን መንግስት እናስወግደው!

**Samson Tamrat ayele/ Schewinfurt**

አምባገነኑ የወያኔ መንግስት የስልጣን መንበሩ ላይ ከተቆናጠጠ ጊዜ ጀምሮ በአገራችንና በህዝባችን ላይ እያደረሰ ያለው የጥፋት ርምጃ ከታሪክ ተጠያቂነት ነፃ አያደርገውም።
ዘረኛው ወያኔ ኢህአዴግ መንግስት በሃይማኖት በጎሳ በዘር መከፋፈሉ ሳያንሰው ዛሬ የሰው ልጅ በሰለጠነበት ዘመን እንኳን በሃይማኖት ጣልቃ በመግባት ሙስሊሙን በመስጊድ ኦርቶዶክሱን በሃይማኖት ገዳማት ላይ ዘመቻ እያደረገ መሆኑን ህዝቡና የገፊቱ ቀማሾች ያውቁታል።
ዛሬ ዛሬ ፖለቲካ በተለያዩ መንገዶች ህብረተሰቡን ማመስ ብቻ ሳይሆን የተማረውን ሃይል በእውቀቱና በሙያው እንዳይሰራ ወያኔ የራሱን ስልጣን ለማራዘም የሚጠቀምበት ስልቱ የመንግስት ሰራተኛው በኑሮውና በስራው የግል ሰራተኛው ማህበራዊ ህይወቱን በማመሰቃቀል በህልውናው ላይ በመምጣት የመከራ ኑሮ እንዲገፉ አድርገውታል።
ስለዚህ የወያኔ መንግስት በተባበረ ክንድ እንዲገታ ኢትዮጵያዊ የሆነ ሁሉ መታገል ይገባዋል።

# ነፃነትን የማያውቅ ነፃ አውጪ

**Tadesse Alemu /Hof**

ምንም እንኳን የወያኔ መንግስት ራሱን ነፃ አውጪ እና ለዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር የታገለ አስመስሎ ቢያቀርብም ሀገራችንና ህዝቦቿ ዛሬም ድረስ በወያኔ የባርነት ቀንበር ሥር እየማቀቁ ይገኛሉ።
ፍትሀዊ እና ነፃ ምርጫ በኢትዮጵያ ምድር የማይታሰብ ሆኗል።ፍርድ ቤቶችና ምርጫ ቦርድ በአዋጅ በተቀመጠላቸው ሥልጣን መሰረት ህዝብን ከማገልገል ይልቅ የወያኔ የፖለቲካ መሣሪያ ሆነዋል።በሀገራችን የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ሙሉ በሙሉ በመንግስት ቁጥጥር ሥር ይገኛል።የነፃው ፕሬስ ጋዜጦችና መፅሔቶች ታግደው ጋዜጠኞቹም ከፊሎቹ በእስር ቤት ቀሪዎቹም በስደት ይገኛሉ።ዜጎች አማራጭ የመረጃ ምንጮችን እንዳይጠቀሙ ታግደዋል።ሙስና የስርዓቱ መገለጫ ሆኗል።በነፃነት መደራጀት፣መሰብሰብና ሃሳብን በነፃነት መግለፅ በአሸባሪነት ያስከስሳል።ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል የለም።የእምነት ተቋማት በነፃነት መሪዎቻቸውን መምረጥ አልቻሉም።
የወያኔ መንግስት በኢትዮጵያ ውስጥ እያደረሰ ያለው ጭቆናና አፈና ፈርጀ ብዙ ሲሆን ይህንን የባርነት ቀንበር ለመሰባበርም የተባበረ ክንድ እና የተቀናጀ ትግል ያስፈልገናል።ነፃነት ለሰፊው ህዝብ!!!

# በህብረት እንቁም!

**Dina Yosef /Klümba**

የኢትዮጵያ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ ለሚደረገው ትግል በስልጣን ላይ ያሉት አምባገነኖች እየሰጡ ያሉት ምላሽ የከፋ መሆኑን በአገሪቱ ላይ እየተከሰቱ ያሉ ሁኔታዎች በግልፅ ያስረዳሉ።

ኢትዮጵያውያንን በዘር እና በሃይማኖት እየከፋፈሉ ጥላቻንና ቁርሾን በማራገብ፣ህዝብን በማጋጨት ብሔራዊ ስሜትን እየሸረሸሩ የሚገኙት ጠባብ ዘረኛ ቡድኖች ፈፅሞ የሀገሪቱን አንድነት የሚፈልግ መንግስት አለመሆናቸውን ህዝቡ በደንብ በመገንዘብ የምርጫ ነፃነቱን ተጠቅሞ ለማስወገድ ቢሞክርም ለይስሙላ የያዙት ዴሞክራሲያዊ መንግስት የመባል ጭንብል በማጥለቅ የህዝብን የስልጣን ባለቤትነት በመካድ ኢ-ዴሞክራሲያዊ በሆነ አካሄድ የህዝብን ድምፅ በመቀማት ፍፁም አምባገነናዊ ሥርዓት መሆኑን በይፋ እያሳየ ይገኛል።
የወያኔ መንግስት እያደረሰ ያለውን ግፍና በደል ለማስወገድ፣የፍትህ ማጣትና የእኩልነት መብት መጓደል ከሚያስከትላቸው የርስ በርስ እልቂት ሀገራችንና ህዝባችንን ለመታደግ ሁሉም የሀገሪቱ ዜጎች ዘርና ሃይማኖት ሳንለይ በህብረት እንቁም!!!

# ወያኔ ሆይ!

## Betewedaj Adenew/ Bayreuth

በሃይማኖት ጉዳይ ውስጥ የሚደረገው ጣልቃ ገብነት ይቁም!

እናንተዬ ወያኔ የሚባለው መንግስት በሃይማኖት ውስጥ እየገባ የሚያደርገውን ጣልቃ ገብነት አሁንም በከፍተኛ ሁኔታ በፊት ከነበረው በበለጠ አጠናክሮ ቀጥሎበታል።እንደ አገራችን አቆጣጠር ከአምና ጀምሮ በሙስሊም ወንድሞቻችን ላይ በከፍተኛ ሁኔታ አጠናክሮ የገፋበትን የሀይማኖት ተቋማትን የፖለቲካ መድረክ ማድረጉን አሁን ደግሞ በኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ላይ እንደወረርሽኝ ተነስቶ አባቶችን ማሠር ማሰቃየት መግደል ተቋማትንና ገዳማትን ማፍረስ ቀጥሎበታል።ይህን የሚያደርገው ደግሞ በማናለብኝነት ነው።

በተዋህዶ እምነት ውስጥ ወያኔ ወደስልጣን እንደመጣ ሀይማኖታችን በማይፈቅደው ወይንም የቤተክርስቲያኗን ቀኖና እና ስርዓት በመጣስ ብፁዕ ፓትሪያርክ አቡነ መርቆርዮስን በመሣሪያ አስገድዶ ከመንበራቸው ማባረሩ ይታወሳል።በዚህም ምክንያት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በሁለት ጎራ ተከፍላ ስትታመስ ከርማለች፥አሁንም እየታመሰች ትገኛለች።

ወያኔ ራሱ ያወጣውን ህገ-መንግስት አንቀፅ 27 ′′ማንኛውም ሰው በግልም ሆነ በስብስብ የፈለገውን እምነት የመከተል እምነቱን የማዳበር የመማር ማስተማር መብት አለው መንግስት ጣልቃ አይገባም′′ይላል።ነገር ግን ይህንን ህግ ወያኔ የሚጠቀመው ከወረቀት አላለፈም።ያሳዝናል።ራሱ ያወጣል እራሱ ይሰርዛል።ይህ ጉደኛ መንግስት የሀይማኖት ጣልቃ ገብነቱን ሊያቆም ይገባል።እግዚአብሔር ተዋህዶ እምነታችንን ይጠብቅ ለሀገራችንን እና ለህዝቧ ሠላም ይስጥልን።አሜን!

# ዲክታተሩ!!!


## Naomi Tesfaye /HochStadt

እ.ኤ.አ. በ2012 ከተሰሩ ምርጥ የሆሊውድ ፊልሞች ውስጥ በምፀታዊ ኮሜዲነቱ አቻ ያልተገኘለት እና በሳሻ ባሮን ኮህን እና አሌክ በርግ ተፅፎ በሌሪ ቻርለስ ዳይሬክተርነት የተተወነው "ዲክታተሩ" /The Dictator/ የተሰኘው ፊልም በቀዳሚነት ይጠቀሳል።በዚህ ፊልም ላይ ዋና ገፀ-ባህርይ ሆኖ የሚጫወተው አድሚራል ጄነራል አላዲን በ100 ሜትር የሩጫ ውድድር ላይ ተሳታፊ ሲሆን አሸናፊነቱን ለማስጠበቅ በጦር መሳሪያ በመታገዝ ውድድሩን ራሱ ያስጀምራል፣የቀደሙትን ይገድላል፣በቅርብ ርቀት የሚከተሉትን ይገድላል እንዲሁም በመግቢያው መስበር ላይ የሚዘረጋውን ሪባን የያዙትን ሰዎች በፍርሃት ተፅዕኖ ውስጥ በማድረግ ከተለመደው አካሄድ ውጪ ሪባኑን ግማሽ መንገድ ድረስ ወደርሱ ይዘው ይሮጣሉ።

በእርግጥ በገሃዱ አለምም በይዘቱ ከዚህ ፊልም ጋር የሚመሳሰል በሀገራችን ኢትዮጵያ በቀጣዩ ሚያዝያ ወር 2005 ዓ.ም. (April 2013) የምርጫ ድራማ እየተዘጋጀ ይገኛል።ይህንንም የምርጫ ድራማ በዋነኛነት እየተወነ ያለው የምናባዊው አድሚራል ጄነራል አላዲን ተምሳሌት የሆነው የወያኔ/ኢህአዴግ መንግስት ሲሆን ከወዲሁ አፋኝ የሆኑ የምርጫ ህጎችን ምርጫ ቦርድ ተብሎ በሚጠራው የወያኔ የድል ሪባንን በያዘው ተቋም አማካኝነት በማውጣት እና የመወዳደሪያ ሜዳውን ለወያኔ ብቻ እንዲመች በማድረግ ከወዲሁ ሠላሳ ሶስት /33/ የፖለቲካ ፓርቲዎች በተፅዕኖ ምክንያት ራሳቸውን ከምርጫው እንዲያገሉ ሲያደርግ የምርጫ ካርድ የወሰዱ ዜጎችንም ከወያኔ በቀር እንዳይመርጡ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ጫና እና ወከባ እየደረሰባቸው ይገኛል።

"ቀን እባብ ያየ፥ሌሊት በልጥ በረየ" እንደሚባለው ከምርጫ-97 ሽንፈት በኋላ የወያኔ መንግስት በየጊዜው በሚያወጣቸው አምባገነናዊ "ህጎች" ምክንያት የፖለቲካ ምህዳሩ ከመጥበቡም በላይ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የሚደረጉ የአካባቢም ሆነ ሀገራዊ ምርጫዎች አለማቀፍ ደረጃቸውን ያልጠበቁ ይልቁንም የይስሙላ ምርጫ ሲሆኑ ለምሳሌ እ.ኤ.አ በ2010 በተደረገው ሀገራዊ ምርጫ ወያኔ 99.6% ድምፅ አገኘሁ በማለት ሀገራዊ ስላቁን አሰምቶናል።

በመሆኑም መላው የሀገራችን ህዝቦች ይህ ወያኔ ራሱ ተወዳዳሪ፥ራሱ አወዳዳሪ ለሆነበት "ምርጫ" ድምጽ መስጠት ለአምባገነኑ መንግስት እውቅና እንደመስጠት፥ብሎም እያደረገ ላለው የግፍ አገዛዝ እና ጭቆና ይሁንታን እንደመስጠት ይቆጠራልና ራሳችሁን ከወያኔ ድራማ እንድትጠብቁ መልዕክቴ ነው።



# The Real Behaviour of Woyane Dictatorship

## Tewodros Abraham /Gross Umstadt

Now adays in Ethiopia there is no problem of shortage of laws. Woyane has for that matter a near perfect conistitution for all to see. It remembers the conistitution of most democratic countries in thewest. The problem is that constitution does not govern the woyane tyrants. They do not obey that law they drafted and enacted. There are also many other international convention that woyane has ratified for the whole world to see. But it does not obey for these laws. There is nothing that can hold woyane accountabele. Woyane is true dictatorship and oppressive. TPLF is suppressing Ethiopian citizens. they tortured and killed lot of people to eliminate the civic movements. They use the conistitution for undercover from the whole world. Plus to this fact, woyane prisoned a lot of journalists and human right activists by the name of terrorism.

So let us come together and force them out by all means now is the time to coolapse woyanes dictatotrial regime for once and for all. We Ethiopian exile should have to do our best and to stop TPLF (WOYANE) dictatorship in Ethiopia.

# Civic Society crackdown in Ethiopia

## Nahom Woldeyohannes / Kirchheim

On January 1,2013 Ethiopia took up its seat on the united nation human right council elected member countries are obliged to uphold the highest standards in the promotion and protec-

tion of human rights. Yet in Ethiopia hundreds of political figures in jails where torture is common and crackdown on the media and civic society is in full swing.

Since the 2005 election the human rights situation in Ethiopia has progressively deteriorated. the government has shut down legitimate political avenues for peaceful protest. and opposition leaders, civic society activists and independent journalists have been jailed or forced to flee like us. Furthermore state driven development policies including large scale agricultural development and programmes have seen communities forcibly relocated from their traditional lands, without adequate consultation or compensation, to village that lack basic service.on the other hand, Ethiopian security forces have in recent years been implicated in crimes humanity and war crimes in the Somali and Gambella regions. But Ethiopia has not only succeded in the stemming criticism at the national level but also internationally.

To sum up , the western governments should urge the weyane regime to release all political prisoners lift unlawful restrictions on civic society the media and stop blocking visit request by UN human right experts. we Ethiopian citizens living abroad should have to pay the ultimate price to collapse TPLF dictatorial regime.

# EPRDF- Stop arresting Journalists

**Hilina Dawit /Nürnberg**

In Ethiopia people are not free to express their political opinions. People may only buy and read censored publications young people are only allowed to do political activities that support the current government. a journalist that criticize the government have to leave the country or other wise are arrested and put in the jail. Many decide to flee from their country. The influence of the ruling party on the Ethiopia media prevents the development of freedem of speech. Even Journalists from abroad that report about political issues have been put into jail. All imprisoned journalists have to be released immediately and the surpression of free speech has to stop. At the end, Ethiopia can finally call itself a true. ''**Democratic**'' republic.

# Freedom and democracy for Ethopian People

**Elsa Hagos /Lahntal**

Freedom and democracy categorically denounces the barbaric killing of innocent civilians and holds H/mariam Desalegne and his associates accountable for the lives lost. The Muslim community in Ethiopia has been waging a legitimate struggle in Ethiopia for the past 1 year The demands are simple and crystal clear thay have asked the regime for freedom of worship and for the right to elect their religious leaders in their own way and place of their own choosing. These rights are protected by the Ethiopian constitution which the regime is obliged to respect.

Ethiopians inside and outside of the country must stand together with our Muslim brothers and sisters. Ethiopian muslims & Christians must stand together as a community to continue the struggle for freedom, justice, democracy and equality understanding and beliving that we live in the context of each other, and acknowledging that the source of our freedom is our collective struggle.

Finally Ethiopia is alarge country that can play a pivotal role in stabilizing the Horn of Africa. But as long as Ethiopia it self is ruled by a beiligerent dictator It could as well be a major force of instability in the Horn of Africa. The United Nations, the United States the European Union, the African union and all peace loving people of the world must condemn the bellicose regime in Ethiopia. And send aclear message that the world does not tolerate this kind of administration again.

# Lets fight woyane´s Tyranny

**Wondwossen Mulugeta/ Rüsselsheim**

It is obvious that the suffering of Ethiopian people increased from day to day, not only journalists convicted under this unfair law of Anti-Terrorism, but also other people on charges of supporting terrorism. In addition to the Anti-terrorism law which is issued in recent years but other laws make the people not free and independent in their own country. The Ethiopian government should end its widening crackdown against oppo-sition politicians and dissidents. Only in the past months, well known journalist like Eskinder Nega, other opposition party members and leaders were arrested in Addis Ababa and in some remote area.

Not only that, the Ethiopian Federal High Court on this year on January convicted three Ethiopian journalists, an opposition leader, and one another under anti-terrorism law that violates free expression and due process rights. This shows that there is no freedom of speech and report in the country. Now we are warning the Ethiopian government should immedi-ately drop the case, release the defendants, and investigate their allegations of torture in detention. In addition, those peo-

ple who are living in the country-side also do not have the right to live permanently in their own land. They are mov-ing from place to place based on the government will. For instance, under its “villagization” program, the government is forcibly relocating approximately 70,000 indigenous people from the western Gambella region to new villages that lack adequate food, farmland, healthcare, and educational facilities. State security forces have repeatedly threatened, assaulted, and arbitrarily arrested villagers who resist the transfers. Who is responsible when innocent people are arrested, tortured, wounded&etc. we have A big responsible so we must fight to stop the Dictatorial power of woyane dictatorship.

# Cowards measures

**Yordanos Hailegiorgis / Lahntal**

In the twenty one years of the TPLF rule, the Ethiopian people and the world at large have witnessed mass killings, targeted killings and indiscriminate killing of the young, old, women and children as young as 8 years old. In 2005 the mass killings in Ethiopia reached its climax when special security forces under the direct order from the late prime minister meles zenawi savagely killed over 200 people as the world watched crulity. when puppet pm Haile Mariam Desalegn took the oath of office and promised to walk on the same path as his predecessor many Ethiopians lowered their expectation of witnessing a free, just and democratic Ethiopia in their life time. the first victims of PM Haile Mariam Desalegn are before a month in Amhara Zone There is no new system or rule by new PM HaileMariam He has no capacity and ability to do new things for Ethiopian people or Ethiopia to create new system and sided to the poor and innocent people of Ethiopia.

# The Failures of Meles

**Tigest Belayneh Zerai/Alsfeld**

After the death of the late primier of Ethiopia Meles Zenawi, ther are a lot of comments regarding his weaknesses and strengtheness. I want to raise some of his failures. I support the Ethiopian democrats view. What Ethiopian democrats will not forgive is the regime's failing to establish a political order and national institutions that have earned the loyalty and respect of the people. The conflation of the regime's interests with the national cause and the use of the security forces to domesticate the population is not a sustainable strategy if Ethiopia is to ever evolve into a vibrant democracy. The ***republic of fear*** must give way to the *rule of law* to thwart a more threatening future.

On the regional front, posterity will not be kind to the Zenawi regime as it has totally squandered the opportunity to forge a more peaceful and collaborative relations with Eritrea and Somalia given the goodwill of these two peoples.

Allowing Somalis the opportunity to rebuild their government and society in a democratic fashion would have eliminated traditional hostilities between the two countries and boosted their mutuality. Further, this approach would have shifted hundreds of millions of dollars from the war machine to development which is desperately needed.

So, Meles made the above cronic problems inside &outside the country. The amazing thing is his predessesor has taken the whole problems like a right way. So, let´s stand to avoid the entire problems of TPLF/EPRDF.

# United Effort Leads to Success

**Robel Weldegebrel (Forchheim)**

It is well known that the Ethiopian people have been struggling for justice and democracy since the beginning of 1970s. The strugge have been led by different political parties and forces in different times. Unfortunately, those political parties and forces which have led the strugge have not achieved their goals of bringing democracy and justice in Ethiopia. Likewise, both the current government and its predecessors have ignored the fundamental demands of the people. Nowadays, especially after the 2005 national election, the political situation of the country has become deteriorating and human rights conditions of the country have been worsening . Following the 2005 election the Ethiopian people and the entire world have witnessed human right abuses in the country such as, mass killings, indiscriminate arrests, tortures, mailing of op position party members and journalists; and democratic right abuses such as, preventing freedom of expressions, association and worshiping. Furthermore, the government has enacted various proclamations which enable itself controlling and restricting civil rights and freedom of speeches of the people. The main reasons why the ruling party

discussions so a sto devise strategies on how these evil acts of the regime would be stopped and on how the Ethiopian people would regain the fundamental rights and freedoms. For this reason, the struggle to bring justice, freedom and democracy to Ethiopia requied united struggleof all stakeholders, which means it needs coalition of all political parties and collective efforts of the Ethiopian people. Because unity is always power and unted struggle is the only way of leading the Ethiopian people to justice, freedom and democracy. ´´Freedom is never voluttarily given by the oppressors; it must be demanded by the oppressed.`` Martin Luther King.

# It is time for Amendment

**Samuel Solomon Wubna/ Bayreuth**

After all those 21 years the Woyane (TPLF) regime is still clinging (sticking) to its out of date, oppressive, discriminative dictatorial rule through out the country. It has been almost half a year since the late dictator Meles Zenawi died TPLF leaders and the state media are busy painting him as the so called ´´Great leader´´ legacy. But the truth is not ridde from the average Ethiopians.

Meles ,who was the master of ruthless politics who considers personal power above anything. He didn't believe for a fraction of a second in the power of the majority of the people. For this reason he had persecuted and imprisoned prominent op position political party leaders; the likes of Dr. Birhanu Nega and Birtukan Mideksa. He reduced freedom of speech and expression to the very minimum. The number of private owned free and neutral news paper publishers shrinked. He even put to jail leading courageous journalists like Eskender Nega, Andualem Arage and many more. The current leaders are continuino this vicious strategy after his death.

But now is the time they consider and act for a change in the best interest of the Ethiopian people. It is new times. It is a big opportunità for reconcillation with the people as well as all the op position political parties which reside either home or are in exile abroad.

It is time for TPLF leadrs to ammend their mistakes and wrongs of the past. They must not lose this opportunity. Change is inevitabile, nothing lasts forever. So we need basic political reform and change before it is too late for them.Freedom, Equality, Democracy and Justice in Ethiopia!!!

# The Magnitude of TPLF's Dictatorship

**Weldekiros Asfaw/Bayreuth**

When a political party under which the power of government is not limited by any law; we call it dictatorship.

Dictatorship has some common features:

(a) Fusion of government and ruling party

(b) Total intolerance towards other center of power.

(c) Extended rule of one party

(d) Abuse of power

(e) Unfair elections

(f) No rule of law

So, let's calibrate the dictatorship of TPLF against the above six parameters:

1. Fusion of Government and Ruling Party: Ruling party uses government resource unrestrictedly and there is no even a thin-air boundary between TPLF led ruling party and government. Then in Ethiopia EPRDF and government are one and the same that could be named interchangeably.

2. Total Intolerance towards other Center of Power: In particular, since 2008 the new directive was enacted on NGOs and Civil Societies. Therefore:

a. It becomes very difficult to have legal registration for civil societies unless they are proved to be pro-the ruling party.

b. Civil Society groups can be illegalized and de-commissioned by only announcement.

For example the famous "Mecha and Tulema" was liquidated just by announcement and they were denied to defend.

3. Extended Rule of One Party: For the last 21 years EPRDF was the only ruling party in Ethiopia. And there is no any glimmer of hope that opposition parties will take over since EPRDF iron curtained the political space. This failure in power alteration has privileged the ruling party for abuse of power, corruption and dictatorship.

4. Abuse of Power: In general the Police, Security and the Army would be responsible to secure the well-being of the society and the sovereignty of the country. In contrast to this fact, these institutions are now serving the ruling party to keep it in power.

We have seen such abuse of power once too often in many occasions like Addis Ababa (2005), Ogaden (2007 upto now), Gambela (2010 upto now), and different parts of Oromia and Amahara region.

5. Unfair Election: Out of 21 years of EPRDF in power, only election-2005 was a fair one. Media access for oppositions was admitted, international observers were invited, opposition party members were not persecuted; and the result showed that how the people of Ethiopia punished EPRDF by its vote. And we all remember how EPRDF used excessive force to maintain its power and rigged vote. And since then election-2010 was a pseudo election with undemocratic features compare to the former.

7. No Rule of Law: The autonomous function of courts is under a big question mark. Besides the judges are under political pressure. We can also see that the constitution has been ignored in many occasions and an arbitrary law prevails over the constitution.

So, when we size up TPLF/EPRDF by all the above dictatorial traits, it is a perfect fit to be called one of the first class dictatorial regimes in the world. And to bring the rule of law, democracy, freedom and equality we have to struggle this dictatorial regime!!!



# ስፖርት



## ለበለጠ ድል እንነሳ

**መስፍን አብርሃ/ጋዜጠኛ/**

29ኛው የአፍሪካ እግር ኳስ ዋንጫ ላይ የተሳተፈው የአገራችን ብሄራዊ ቡድን ለተሳትፎ ብቻ ሳይሆን አቅሙን ለማሳየት እድሉን ተጠቅሞበታል።በእርግጥ ቡድናችን የሆነ ተዓምር ይፈጥራል ብለን አስበን ሳይሆን ከተሳተፈ አይቀር ለተሳትፎ ብቻ መሆን የለበትም የሚጫወተው ብለን ነበር።

እንዳልነውም የቡድናችን ከፍተኛ ችግር የነበረው ምንም እንኳን የአሰላለፍ ችግር ቢሆንም ዋነኛው ግን የዓለም አቀፍ እግር ኳስ መድረክ ልምድና ስርዓትማጣት ሆኖ አግኝተነዋል።

የቡድናችን ተሰላፊዎች የተሻለ ውጤት ለማምጣት ካላቸው ፍላጎትና ጉጉት ያባከኗቸው ኳሶች ሁሌም እንደሚባለው የአጨራረስ ችግራችንን አጉልቶ ያሳየን ቢሆንም የኣለምአቀፉ እግር ኳስ መድረክ ልምድ ማነስ*ፕሮፌሽናል የመሆን ችግር*ግን ትልቁን ዋጋ አስከፍሎናል።

ከዛምቢያና ከናይጄሪያ ጋር በተጫወትን ጊዜ የሁለቱ ግብ ጠባቂዎቻችን ብቃት ከሌሎቹ የአፍሪካ ቡድኖች በረኞች ጋር ምንም የማይተናነስ በተክለ-ሰውነትም ቢሆን አቻ ቢሆኑም፤በስነምግባር ጉድለት ግን የሚያህላቸው አልተገኘም።ለተፈጠረው ሽንፈትም ከ50 በመቶ በላይ ምክንያቱ ይኸው ይሆናል።ካምቦሎጆ ባሉ አልቢትሮች ላይ የለመድነውን ትርፍ ቃል መነጋገር ዓለምአቀፍ መድረክ ላይ እንደማይሰራ ልንማርበት ይገባል አራት ነጥብ።

በተጨማሪም  የአዳነ ግርማና የአስራት ተጎድቶ ከሜዳ መውጣት እንዲሁም የሳላህዲን ብቸኝነት ቡድናችን ዙሩን እንዳያልፍ ደንቃራ ሆነውበታል።ቢሆንም ግን በውጤቱ አልተከፋነም።ልንከፋም አይገባም።የ29ኛው የአፍሪካ እግር ኳስ ዋንጫ ተሳትፎ መቼም የማይገኝ ከፍተኛ ልምድ አስገኝቶልናልና።ደግሞም እኛ ብቻ ሳንሆን በመጀመሪያው ዙር ሰባት አገሮችም ወደ አገራቸው ለመመለስ ተገደዋል።

ስለሆነም በውጤቱ ሳንዘናጋ ለዓለም ዋንጫ ማጣሪያና ከአሁን በሁዋላ በየሶስት ዓመቱ ለሚከናወነው የአፍሪካ ዋንጫ ራሳችንን ብቁ አድርገን ለበለጠ ድል መነሳሳት ይጠበቅብናል።ቡድኑ የጀግና አቀባበል ሊደረግለትም ይገባል።መደረጉም ተገቢ ነው።ታሪክ የሰራ ነውና።

ከሁሉም በላይ ግን ደቡብ አፍሪካ የምትገኙ ኢትዮጵያውያን የፈለገ የፖለቲካ ልዩነት ቢኖራችሁም ኳሳችንን በአንድነት በመደገፋችሁ ኮራንባችሁ።አልሆነልንም እንጂ 12ኛ ተጫዋቻችን እናንተ ነበራችሁ።መልካም ዕድል ዛሬም ነገም ለዘላለሙ ለኢትዮጵያችን የጥላ መፅሄት ምኞት ነው።






በኢትዮጵያ ምርጫ ሲነሳ **The Dictator** የሚለው ፊልም አብሮ ይነሳልና ፊልሙን ላላያችሁት የዚህ እትም ግብዣችን ይሁናችሁ። በነገራችን ላይ ይህ ፊልም በ2011 እንደወጣ አዲስ አበባ የሚገኘው ማቲ ሲኒማ ሊያሳየው ሲል በኢህአዴግ ባለስልጣናት መታገዱ ይታወሳል።

---



**በአፍሪካ ዋንጫ ዓለምን ያስደመሙት ብርቅዬዎቹ ኢትዮጵያውያን በደቡብ አፍሪካ። ስለእውነት ኮራንባችሁ !!!**




# ጥላ መፅሄት ስድስተኛ እትም

ጥላ መፅሄት ስድስተኛ እትሟን ይዛ April 30/2013 ለንባብ ትበቃለች። ስለዚህ አዲስና ነባር ደንበኞቻችን በተለመደው አድራሻችን ታገኙናላችሁ። በመፅሄታችን ላይ ያላችሁን አስተያየትና መልዕክቶች ሁሉ እስከ April 25/2013 ድረስ ልታደርሱን ትችላላችሁ።

ለበለጠ መረጃ የስልክ መስመራችንን መጠቀም ይቻላል።

**WIR SIND IMMER FÜR SIE DA!**

**አድራሻችን**

**Mesfin Abraha**
**Löhrgasse 4**
**36251 Bad Hersfeld**
**E-Mail: tilamagazine@yahoo.de**
**Web-Site: tilamagazine.yolasite.com**
**Tel.No. 0152- 22195567**
**0176- 59384456**
**0176- 68830082, 0176-71668780**

**TILA MAGAZIN IST EURE MAGAZIN!**